# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ብሔራዊ የዶሮ ሀብት ልማት ፖሊሲ

**ታህሳስ 2011ዓ.ም**

አንድ ዕንቁላል በቀን ለሁሉም ኢትዮጵያዊ !!

1. መግቢያ ..... 3
2. የፖሊሲው አስፈላጊነት፣ ራዕይ ፣ ተልዕኮ እና ወሰን ..... 5
2.1. የፖሊሲው አስፈላጊነት ..... 5
2.2. ራዕይ ..... 6
2.3. ተልዕኮ ..... 6
3. የፖሊሲው ዓላማ ..... 7
3.1. ዝርዝር ዓላማዎች ..... 7
4. የሀገራችን የዶሮ ሀብት ልማት ገጽታ ..... 7
4.1. የዶሮ እርባታ ስርዓት (ሥልተምርት) ..... 8
4.2. እሴት ሰንሰለት ..... 10
4.3. ለዶሮ ሀብት ልማት ምቹ ሁኔታዎችና መልካም አጋጣሚዎች ..... 10
5. የፖሊሲ አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች ..... 12
5.1. የዶሮ እርባታ ሥርዓት ማሻሻል ..... 12
5.2. የዝርያ አቅርቦት ማሻሻል ..... 13
5.3. የዶሮ መኖ አቅርቦት ..... 21
5.4. የዶሮ ጤና ..... 23
5.5. ምርት ማቀነባበር ሂደት ..... 27
5.6. ምርምርና ቴክኖሎጂ ስርጸትከ ትስስርማጠናከር ..... 30
5.7. በዶሮ እርባታ የማህበረሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ስለማሳደግ ..... 32
5.8. አቅም ግንባታን በተመለከተ ..... 35
5.9. ግብይት ..... 36
5.10. መሰረተ ልማት ..... 37
5.11. ኢንቨስትመንት ..... 38
6. ተጓዳኝ ጉዳዮች ..... 39
6.1. ሥርዓተ ጾታ ..... 39
6.2. የአካባቢ ጥበቃ እና የማህበረሰብ ደህንነት ..... 39
6.3. ሥነ ምግብ ..... 40
6.4. የአገር በቀል ዕውቀት ..... 41
7. ከፖሊሲው የሚጠበቅ ውጤት ..... 41
8. ተቋማዊ ሁኔታና የህግ ማዕቀፍ ..... 42
8.1. ተቋማዊ አደረጃጀት ..... 42
8.2. የግል ተቋማት ..... 43

9. የበጀት ድጋፍ.....43
9.1. ለመንግስት ተቋማት የሚደረግ የበጀት ድጋፍ.....43
9.2. ለግል ተቋማት የሚደረግ የበጀት ድጋፍ.....44
10. ክትትልና ግምገማ.....44

## 1. መግቢያ

ሀገራችን በእንስሳት ሀብቷ ከአለም ሀገራትም ሆነ ከአፍሪካ ሀገራት አንጻር በግንባር ቀደምትት የምትታወቅ ሲሆን ለዶሮ ሀብት ልማት የተመቸ ሁኔታ እንዳላትና በተለያየሥነ-ምህዳር መርባት የሚችሉ የዶሮ ሀብት መኖሩ የሚታወቅ የግብርናው ዘርፍ ለሀገሪቱ አጠቃላይ የምርት እድገት 42% የሚያበረክት ሲሆን የእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፉ ከአጠቃላይየሀገሪቱምጣኔ እድገት 19በመቶድርሻእንዳለውመረጃዎችይጠቁማሉ።

ሀገሪቷ ከዶሮ ሀብቷ በየአመቱ የዶሮ እንቁላልምርት1230 ሚሊየን እና የዶሮ ስጋ 86.4 ሺህቶን እንደሆነ ሲገመት ዓመታዊ የሀገሪቱ ነፍስ ወከፍ ፍጆታ እንቁላል 0.5ኪሎ ግራምና የዶሮ ስጋ ደግሞ 0.6ኪሎ ግራም ብቻ እንደሆነ ያሳያል። የሀገራችን የዶሮ እንቁላልና ሥጋ የነፍሰ ወከፍ ፍጆታ ከሰሀራ በታች ከሚገኙ የአፍሪካ አገራት የነፍስ ወከፍ ፍጆታ የዶሮ ስጋ 4.5 ኪሎ ግራም እና እንቁላል 2.3 ኪሎ ግራም እና ከዓለም የነፍስ ወከፍ ፍጆታ የዶሮ ስጋ 13.8 ኪሎ ግራምና እንቁላል 8.9 ኪሎ ግራም ጋር ሲነፃፀር በዝቅተኛ ደረጃ መገኘቱ እንደ ውስንነት የሚታይ ጉዳይ ነው። ይህ አኃዝ የሚያሳየው የዶሮ ምርት ዕድገት ከህዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር ስለማይጣጣም የነፍስ ወከፍ ፍጆታው ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል። ከዚህ በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ካላቸው የአእዋፍ ዘሮች መካከል በሀገራችን የዶሮ ዘሮች ብቻ ለኢኮኖሚያዊም ሆነ ለምግብነት ጥቅም ላይ እየዋሉ የሚገኙ የአእዋፍ ዘሮች እንደ ዳክዬ፣ ጅግራ፣ ሰጎንና የመሳሰሉት ኢኮኖሚያዊ የአእዋፍ ዘሮች ላይ በስፋት በመስራት ሀገራዊ የሆነ እንቁላልና ስጋ ምርት እድገት አስተዋፅኦ እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል።

የዶሮሀብትልማቱ በሀገር ውስጥ ጉልህ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንዳይኖረውና እንዳይስፋፋ ከሚያደርጉ ዋና ዋና ችግሮች መካከል የሀገር በቀል የዶሮ ዝርያዎች ምርታማ አለመሆንና የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች አቅርቦት ውስንነት ፣የመኖ እጥረት፣ የዶሮ በሽታዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፉ መምጣት፣ የኤክስቴንሽንና የምርምር አገልግሎት ትስስር አለመጠናከር ፣በሙያው የሰለጠነ የሰው ሀይል እጥረት፣ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ውስንነት፣ የገበያ ስርዓት አለመዘርጋት፣ የመገልገያ መሳሪያዎች አቅርቦት ውስንነት፣ በዶሮ ልማት ዘርፉ የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ ውስን መሆንና ተገቢውን ትኩረት ለልማቱ አለመሰጠቱ ሊጠቀሱ የሚችሉ ተግዳሮቶች ናቸው።

የዶሮ ሀብት ልማቱ በሀገራችን ለዜጎች ማበርከት የሚችለው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታበተለይም የምግብና ስነምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ለስራ እድል ፈጠራ፣ ገቢ ማመንጫ መንገድና ድህነትን ለመቀነስ፣ ጤናማና አምራች ሀይል ለመፍጠር በሚደረገው ርብርብ ላይ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። የዶሮ እርባታ ስራ በእያንዳንዱ ቤተሰብ በተለይም በሴቶችና ወጣቶች በቀላል ወጪ መካሄድ መቻሉ ለዜጎች መከፈት የሚችለውን የስራ ዕድል በእጅጉ የጎላ ያደርገዋል።በኢንዱስትሪውም መስክ ቢሆን ዘመናዊ የዶሮ እርባታ ስርዓት ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ባለው ኢንዱስትሪ መክፈት የሚቻልበት በመሆኑ ለሀገር ኢኮኖሚ የውጭ ምንዛሪን ማስገኘት የሚችልና በአሁኑ ጊዜ ዶሮና የዶሮ ምርት ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ወደሀገር ውሰጥ ለማስገባት የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ማስቀረት የሚችል እና ሰፊ የስራ ዕድል ከመፍጠር አንጻርም በውስጡ ከፍተኛ የሰው ኃይል ማሰማራት የሚቻልበት መስክ ነው። በዚሁ

መሰረት የዶሮ ዘርፉን ለሀገር እድገትና ብልፅግና ያለውን ሁለንተናዊ ጠቀሜታ ለማጠናከር እና እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶችን ለመፍታት ይህ የዶሮ ሀብት ልማት ፖሊሲ ተዘጋጅቷል።

## 2. የፖሊሲው አስፈላጊነት

ሀገራችን ለዶሮ ሀብት ልማት የተመቸ ሁኔታ እንዳላትና በተለያየሥነ-ምህዳር መርባት የሚችሉ የዶሮ ሀብት ቢኖሯትም  ከዶሮ ምርት ውጤቶች ተጠቃሚነት አንፃር ሲታይ ምርቶችዋን በአግባቡ ከማይጠቀሙ ሀገራት ተርታ ትመደባለች። በዶሮ ልማት ዘርፉ የሚስተዋሉትን ምቹ ሁኔታዎችና መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም እምቅ ሀብቱን ለማልማት፣ ለመጠቀምና ለመጠበቅ የሚያግዙ ፖሊሲዎችና  አስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ካልተቻለ በስተቀር መንግስት የምግብና ስርዓተ-ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ለወጣቱ የስራ እድል መፍጠርእና በአጠቃላይ ለድህነት ቅነሳ የተያዙ ግቦች ለማሳካት ከፍተኛ ጋሬጣ ሆነው ይቀጥላሉ፡በተለይም የዶሮ ሀብቱን በመደገፍ የህብረተሰቡን የምግብና ስነ ምግብ ፍላጎት የሚጠበቀውን ድርሻ  ለማበርከት፣ ለዶሮ እርባታ ተስማሚ የሆኑ የዶሮ ዝርያዎች በበቂና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚያቀርቡ የዶሮ ዝርያ ማባዣ ማዕከላት እንዲስፋፉ፣ ጥራት ያለው የዶሮ መኖ አቅርቦትን ለማሻሻል፤ ለመኖ የሚውሉ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ለማመቻቸት ፣ የመኖ ጥራት ቁጥጥር ስርዓትን  እንዲሁም የመኖ ይዘትና ጥራት ምርመራ አቅጣጫ ለማኖር፣ የዶሮ በሽታን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት፣ የግል ባለሃብቱን በዚህ ዘርፍ እንዲሰማራ ለመደገፍ እና ለማበረታታት፣ ዘርፉ ለአደጋ ተጋላጭ በመሆኑ ለብድር ሰጪ ተቋማትም ያላቸውን ስጋት በመቀነስ አርቢው ወደ ዶሮ ልማት እንዲሳብና ያለውን አቅም ሙሉ በሙሉ እንዲጠቀም ለማስቻል፣ የልማቱ ተዋናዮችን አቅም ለማሳደግ እና የመሠረተ ልማት ግንባታን ለማስፋፋት፣ በዶሮና በዶሮ ውጠቶች ላይ እሴት በመጨመር እና የግብይት ስርዓቱን በማሻሻል ለተጠቃሚው ማድረስ ላይ ተገቢውን ቁጥጥር ለማድረግ፣ የምርምርና ኤክስቴንሽን ተደጋጋፊነትና ተመጋጋቢነት በማጠናከር ለግል ባለሀብቱም ጭምር የኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ በመስጠት የቴክኖሎጂ ማፍለቅ፣ ሽግግርና አጠቃቀምን ለማስፋት ይህን የዶሮ ሀብት ልማት ፖሊሲ ማዘጋጀት አስፈልጓል።

### *2.1.* ራዕይ

የኢትዮጵያ የዶሮ ሀብት ልማት ኢንዱስትሪን በማዘመን በቂ መጠንና ጥራት ያለው  የዶሮ ምርት በማምረት የምግብና ስነ-ምግብ ዋስተናው የተረጋገጠ ህብረተሰብ ተፈጥሮ ማየት ነው።

### *2.2.* ተልዕኮ

የዶሮ እርባታ ሥርዓት፣ የዝርያ አቅርቦትን፣ የዶሮ መኖ አቅርቦትን፣ የዶሮ ጤና አጠባበቅን፣ አጠቃላይ የዶሮ ስርጪት ሰንሰለት ተዋናዮች የአቅም ግንባታ ሥርዓዎቸን በማሻሻል የዶሮምርትናምርታማነትን በማሳደግ ሀገሪቷ ለምግብና ስነ-ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፣ ለድህነት ቅነሳ እና መካከለኛ ገቢ ለመግባት ለምታደርገው ጥራት የዶሮ ሀብት ዘርፍ ጉልህ ድርሻ እንዲኖረው ማድረግ ነው።

## 3. የፖሊሲው ዓላማ

የዚህ ፖሊሲ ዋና ዓላማ የዶሮ ሀብት ልማት ኢንዱስትሪን በማዘመን የዶሮ ልማት ዘርፉ ለምግብና ሥነ ምግብ ዋስትናንማረጋገጥ እና ለስራ እድል ፈጠራ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ለማሻሻል ነው።

### 3.1. ዝርዝር ዓላማዎች

1. የዶሮ ልማት የሚሻሻልበትና ሀገሪቱ ከዘርፉ የምታገኘው ማህበራዊ፣ ፖሊቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ የልማትና የምርምር ስራዎችን መምራት
2. የዶሮ ልማት ዘርፉ ለምግብና ስነ ምግብ ዋስትና መረጋገጥ ያለውን እምቅ አቅም አውጥቶ ለመጠቀም ነው
3. የሀገሪቱን የዶሮ ሀብት ዓይነት ፣ መጠንና ስርጭት ማሳደግ፣ ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያላቸውን የአእዋፍ ዘሮችን፣ ማልማት፣ መጠበቅና መጠቀም የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት፣
4. ለዶሮ እርባታ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ማለትም የመኖ፣ የጤና እና የእርባታ ቁሳቁሶች እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ግብዓቶች አቅርቦት፣ የጥራት ደረጃቸውን እና ውጤታማታቸውን ማረጋገጥ፣

# 4. የዶሮና የዶሮ ምርት ከውጪ ሀገርም ሲገቡም ሆነ ሀገር ውስጥ ተመርተው ለገበያ ሲቀርቡ የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲቀርቡ የጥራትና ደህንነት ማረጋገጫ ስርዓቶችን ለመዘርጋት፣የዶሮና የዶሮ ምርትን እሴት ለመጨመርና ደረጃውን የጠበቀ የገበያ ትስስር ስርዓት የሚፈጥሩ አሰራር ስርዓቶችን ለመዘራገት የፖሊሲዉ ወሰን

ይህ ፖሊሲ "ብሔራዊ የዶሮ ሀብት ልማት ፖሊሲ" ተብሎ ይጠራል። መነሻ ያደረገውም የህግና የሥነ-ምግባር መሰረት በሆነው በሀገሪቱ ህገ-መንግሥት የሰፈረውን የዜጎችን ደህንነትና መብት ማስጠበቅ ሲሆን አዘገጃጀቱም ከሴክተሮች ፖሊሲዎችና ስልቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ ነው። የፖሊሲው ወሰን አጠቃላይ በዶሮ ምርትና ምርታማነት ትግበራን ለማበረታታትና ተያያዥነት ያላቸውን የትግበራና አስተዳደራዊ ስልቶችን ለመዘርጋት የፖሊሲ መሰረት ይሰጣል።

ፖሊሲው ሁሉንም ቁልፍ የሆኑ የዶሮ ምርትና ምራታማነትን ለማሻሻል ወሳኝ የሆኑ እንደ የዶሮ እርባታ ስርዓትን ለማዘመን፣ የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያ አቅርቦትን ለማሻሻል፣ የዶሮ መኖ አቅርቦትን፣ የዶሮ ጤና አጠባበቅን፣የአቅም ግንባታ እና የመሰረተ ልማት ዝርጋታን ለማሻሻል እና ለማጠናከር ጥረቶች አጠቃላይ ማዕቀፍ ይሰጣል።

## 5. የፖሊሲው እሴቶች

ብሔራዊ የዶሮ ሀብት ልማት ፖሊሲ

- ሕብረተሰቡን ማዕከል ያደረገ – የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ቅድሚያ መስጠት።

- ቅንጅታዊነት—ሁሉም ባለድርሻ አካላት በፖሊሲው ትግበራ ላይ በተቀናጀ መልኩ እንዲሳተፉ ማድረግ
- አሳታፊነት—በሁሉም የውሳኔ ሰጪነት እርከኖች በግልም ሆነ በጋራ በዕቅድ ዝግጅት፣ ትግበራና ግምገማ ማሳተፍ።

ተጠያቂነት—ለስራዎች ቁርጠኛ መሆንና ኃላፊነት በመውሰድ ግልፀኝነት በተሞላበት አግባብ ውጤቶችንም ማሳወቅ።

ሙያተኝነት—በስልጠና የተገኘውን ዕውቀት እና ክህሎት አጣምሮ በመያዝ መተግበር መቻል።

ፍትሃዊነት—ሚዛናዊነትን ማስፈንና አድሏዊነትን እና ሊወገዱ የሚችሉ ልዩነቶችን ማስወገድ።

ልህቀት – የመጠቀ/እጅግ የተሻለ የመሆን ብቃት።

እኩልነት—በተመሳሳይ ማህበራዊ ቡድን ውስጥ ያሉ ሰዎች በተመሳሳይ ደረጃ የመታየትና የመገልገል መብት።

ምላሽሰጪነት— የማህበረሰቡን ፍላጎትና ችግር በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በፍጥነትና አዎንታዊ በሆነ መልኩ ምላሽ መስጠት።

## 6. የፖሊሲ አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች

### 6.1. የዶሮ እርባታ ሥርዓት ማሻሻል

በሀገራችን የዶሮ እርባታ በሶስት የተለያዩ እርባታ ሥርዓቶች ላይ ተመስርቶ በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን እነዚህም የጭሮሽ እርባታ፣ የተሻሻለ የቤተሰብ ዶሮ እርባታ እና ስፔሻላይዝድ የዶሮ እርባታ ሥርዓቶች ናቸው። ከ 90.5 ፐርሰንት በላይ የሚሆነዉ የእርባታ ሥርዓት በጭሮሽ እርባታ ላይ የተመሰረተ፣ እጅግ ኋላ ቀር የአረባብ ዘዴ የሚከተልና ዝቅተኛ የምርታማነት ደረጃ ያላቸው የሀገረ ሰብ ዶሮ ዝርያዎችን በመያዝ የሚካሄድ በመሆኑ ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በእጅጉ ዝቅተኛ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። በመሆኑም በሀገሪቱ ከዘርፉ ልታገኘው የምትችለው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እውን ለማድረግ የእርባታ ስርዓቱ በተለይም የጭሮሽ እርባታ ስርዓቱን ወደ ቤተሰብ እና ስፔሻላይዝድ ስርዓት ደረጃ በደረጃ ማሻሻልና፣ እስፔሻላይዝድ የእርባታ ስርዓቱ ደረጃ (ዝቅተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ) እና ስታንዳርድ እንዲወጣለትበማድረግ ተገቢውን ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲመቻች ማድረግ ያስፈልጋል። ይህም ለመተግበር የሚከተለዉ የፖሊሲ አቅጣጫ ተቀምጧል።

ፖሊሲ፦ ኢትዮጵያለተለያዩ የዶሮ ዕርባታ ሥርዓቶች ተስማሚ የሆኑ ስታንዳርዶች እንዲኖራት ይደረጋል።

ስትራቴጂዎች፦

ሀ. ለተለያዩ የዶሮ እርባታ ሥርዓቶች ማለትም የጭሮሽ እርባታ፣ የተሻሻለ የቤተሰብ ዶሮ እርባታ እና ስፔሻላይዝድ የእርባታ ሥርዓቶች ውስጥ መርባት የሚገባቸው የዝርያ ዓይነቶች፣ የዶሮ ቁጥር መጠን፣ የመጠለያ ዲዛይን፣ የባዮሴኪዩሪቲ ፕሮቶኮልና የመሳሰሉት ስታንዳርዶች እንዲወጡ ማድረግ።

ለ. የጭሮሽ የእርባታ ዘዴ ከማዘመን አኳያ ዶሮ አርቢ አርሶ አደሮች በሀገር ዉስጥ በመረጣ የተሻሻሉ ወይም በማዳቀል የተገኙ 25 ጥምር ጠቀሜታ ያላቸዉ የዶሮ ዝርያዎች እንዲያረቡ፣ለዶሮዎች መጠለያ፣ መመገቢያና መጠጫ ከአካባቢ ቁሳቁስ እንዲያዘጋጁናበቀን ከሚያገኙት የጭሮሽ መኖ በተጨማሪ 50 በመቶ ተጨማሪ የተመጣጠነ መኖ እንዲሰጡናዶሮዎች የሚዉሉባቸዉ ማሳዎች ላይ የተሻሻሉ እንደ አልፋ አልፋ ያሉ ለዶሮዎች ገንቢ ንጥረ ነገር ያላቸዉ የመኖ ዝርያዎች እንዲዘሩና ለዶሮዎቹ የቀን መዋያ የሚሆን ቦታ በሽቦ አጥር እንዲያጥሩ ማድረግ።

ሐ. የተሻሻለ የቤተሰብ እርባታውን ከመተግበር አኳያ ለሀገራችን ተስማሚ የሆኑ፣ የዶሮ ምርትና ምርታማነት ሊጨምሩ የሚችሉ የደሮ ዝርያዎችን እንደዚሁም ለአርቢዉ ህ/ሰብ ከፍተኛ ትርፍ ሊያስገኙ የሚችሉ ሌሎች አዳዲስ የዶሮ እርባታ ሥርዓቶች ከሌሎች ሀገሮች ልምድ በመቅሰም የተመረጡ አዳዲስ የአረባብ ዘዴዎች በሀገራችን በማስተዋወቅ ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ይደረጋል።

### **6.2.** የዝርያ አቅርቦትን ማሻሻል

#### **6.2.1.** ለተለያዩ የዶሮ ዕርባታ ዘዴዎች ተስማሚና አዋጭ የሆኑ ዝርያዎችን ማፍለቅ

ሀገራችን በተለያየ ስነምህዳር ሊረባ የሚችል የዶሮ ሀብት ቢኖራትም አብዛኞቹ ዶሮዎች ሀገር በቀል የሆኑና ዝቅተኛ ምርት የሚሰጡ በመሆናቸዉ በአሁኑ ሰዓት በዋናነት የዝርያ አቅርቦቱን ለማሻሻል ዝርያዎችን ከዉጭ በማስገባትና በማላመድ መጠቀም እየተሰራበት ይገኛል። ይሁንና ይህ አካሄድ ከፍተኛ የዉጭ ምንዛሪ የሚጠይቅና ተተኪ ዝርያዎች ሁሌም ከዉጭ ሀገራት እንድናስገባ የሚያስገድድ ነዉ። በመሆኑም ይህንን ችግር ለመቅረፍ የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች በሀገር ዉስጥ በቀጣይነት እንዲመነጩ ማድረግ ያስፈልጋል።ይህንንም ከግብ ለማድረስ ብሔራዊ የእንስሳት የርቢ ፖሊሲና ስትራቴጂ 2009 ሰነድ ላይ ከተቀመጠው አቅጣጫ የተወሰኑ ጉደዮች ላይ ተጨማሪ በማድረግ የሚከተለዉ የፖሊሲ አቅጣጫ ተመላክቷል።

ፖሊሲ፡- ሀገራችን ለተለያዩ የዶሮ ዕርባታ ዘዴዎች ተስማሚና አዋጭ ዝርያዎች ለማፍለቅ የሚያስችሉዉስጣዊና ዉጫዊ የዝርያ ማፍለቂያ ዘዴዎች ትጠቀማለች።

ስትራቴጂዎች፡-

ሀ. ለጭሮሽ ዕርባታ ዘዴ ተስማሚ የሆኑ ጥምር ጠቀሜታ ያላቸዉ ዝርያዎች ለማፍለቅ የሀገርሰብ ዶሮዎች በመረጣ ማሻሻል ወይም በማላመድ ከተገኙ ጥምር ጠቀሜታ ካላቸዉ ዝርያዎች ጋር ማዳቀል (እስከ 50 ፐርሰንት የደም መጠን)

ሐ. ለተሻሻለ የቤተሰብ ዕርባታ ዘዴ ተስማሚ የሆኑ ጥምር ጠቀሜታ ያላቸዉ ዝርያዎች ለማፍለቅ የሀገርሰብ ዶሮዎች በመረጣ ማሻሻል ወይም በማላመድ የተገኙትን መጠቀም ወይም በማላመድ የተገኙትን በማዳቀል ሴንቴቲክ ዝርያ ማዉጣት

ሐ. ለስፔሻላይዝድ ዕርባታ ዘዴ ተስማሚ የሆኑና ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ የእንቁላል ወይም የሥጋ ዝርያዎቸ ለማፍለቅ 1ኛ) የመስራችና ቅድመ መስራች የእንቁላል ወይም የሥጋ ዝርያዎች በቀጥታ ከዉጭ በማስገባት አባዝቶ መጠቀም፣ 2ኛ ከዉጭ ከገቡት ዝርያዎች በማዳቀል ሴንቴቲክ ዝርያ ማመንጨት፣

**6.2.2.** የተሻሻሉ የዉጭ ሀገር የዶሮ ዝርያዎች ወደ ሀገር ዉስጥ በማስገባት ማላመድ፣ ማራባትናጥቅም ላይ ማዋል

የሀገር ሰብ ዶሮዎች አካባቢን የተላመዱና በሽታ የመቋቋም አቅም ያላቸዉ ቢሆኑም ለእንቁላል፣ ለሥጋ እንደዚሁም ለጥምር ጠቀሜታ ያላቸዉ ምርት በጣም ዝቅተኛ ነዉ።

በዚህም ምክንያት የተሻለ ምርት የሚሰጡ የዶሮ ዝርያዎች ኩብዙ አስርት አመታት ጀምሮ ከዉጭ በማስገባትና በማላመድ በሀገር ዉስጥ በጥቅም ላይ እየዋሉ ይገኛሉ። ሆኖም በተለያዩ ጊዜያት በግል ባለሀብቶችና እንዲሁም የመንግስት ዶሮ ማባዣ ማዕከላት ከዉጭ የገቡ የዶሮ ዝርያዎች ስርጭትና ምርታማነት በዉል አይታወቅም። በመሆኑም ያሉትን በጥናት ለይቶ ማወቅና ለሀገራችን ተስማሚ የሆኑ ዝርያዎችን ሀገር ዉስጥ አስገብቶ በማላመድ ለእንቁላል፣ ለሥጋ እንደዚሁም ለጥምር ጠቀሜታ ከፍተኛ ምርት ማግኘት ይቻላል።

ይሁንና በሀገራችን የእንቁላልና የዶሮ የሥጋ ምርትና ምርታማነት ለማሻሻል የዉጭ ሀገር የዶሮ ዝርያዎች ወደ ሀገር ዉስጥ በማስገባት ጥቅም ላይ ከመዋላቸዉ በፊት ተገቢዉ ጥንቃቄ ካልተደረገና ጠቀሜታቸዉ ቀደም ተብሎ ካልተጠና በሀገሪቷ የዶሮ ዝርያዎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። እንዲሁም ከሀገር ውስጥ ለዘር በጫጩት፣ በለማ እንቁላል፣ በአባለዘር ወይም በማንኛዉም መልኩ የሚወጡ የዶሮ ዝርያዎች በአግባቡ ታውቀውና ተመዝግበው እንዲወጡ ማድረግ ሀገሪቷም ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ በዓለም አቀፍ የጀነቲክ ሀብት ልዉዉጥ ደንብ መሰረት ተገቢው ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል።

ከላይ ለተጠቀሱት ችግሮች ተገቢውን የመፍትሄ ለመስጠት ይቻል ዘንድ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል።

ፖሊሲ፦ ሀ)በተለያየ ጊዜያት በግል ባለሀብቶችና እንዲሁም በመንግስት የዶሮ ማባዣ ማዕከላት ወደ ሀገራችን የገቡ የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች ስርጭትና ምርታማነት ተጠንቶ እንዲለዩ ይደረጋል።

ለ) ለስፔሻሻላይዝድና ለተሻሻለ የቤተሰብ ዶሮ እርባታ ስርዓት የሚውሉ የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች ወደ ሀገር ዉስጥ አስገብቶ በማላመድና በማባዛት ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ይደረጋል፡

ስትራቴጂዎች፡-

ሀ. በሀገር ዉስጥ የሚገኙ የእንቁላል፣ የሥጋ እና ጥምር ጠቀሜታ ያላቸዉ የዉጭ የዶሮ ዝርያዎች ስርጭታቸዉን፣ ምርታማነታቸዉንና ብዛታቸዉን በጥናት መለየት፣

ለ. በመላመድ ብቃታቸዉ፣ በእንቁላል፣ በሥጋ እና በጥምር ጠቀሜታቸዉ እንደዚሁም በሌሎች ጠቃሚ ባህሪያቸዉ የተመረጡ የዉጭ ሀገር የዶሮ ዝርያዎችን ከዉጭ በጫጩት፣ በለማ እንቁላል ወይም በአባለዘር መልኩ በማስገባትና በማላመድ በተፈጥሮና በሰዉ ሰራሽ ዘዴዎች እንዲራቡ ማድረግ፣

ሐ. በመላመድ የተገኙ ለእንቁላል፣ ለሥጋ እና ለጥምር ጠቀሜታ ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ የዉጭ የዶሮ ዝርያዎች መስራች ዘር ማራቢያ ማዕከላት በባለሀብቶች፣ በማህበራትና እንደ አስፈላጊነቱ በመንግስት ተስማሚ በሆኑ አካባቢዎች በማቋቋም ተራብተዉ እንዲሰራጩ ማድረግ፣

ፖሊሲ፦ ከዉጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ ለዘር በሚገቡና ከሀገር ወደ ዉጭ ለዘር በሚወጡ የዶሮ ዝርያዎች ላይ ቁጥጥር ይደረጋል።

ስትራቴጂዎች፡-

ሀ. ለሀገራችን ተስማሚ የሆኑ የእንቁላል፣ የሥጋ እና ጥምር ጠቀሜታ ያላቸዉ የዶሮ ዝርያዎች ከዉጭ ሀገር ለዘር በለማ እንቁላል፣ በጫጩት እና በአባለዘር በሚገቡበት ጊዜ በአግባቡ ታውቀውና ተመዝግበው እንዲገቡ ቁጥጥር ማድረግ፣

ለ. የዶሮ ዝርያዎችን ከዉጭ ሀገር አስገብተዉ እርባታ የሚያካሄዱ ድርጅቶች የርቢ ዶሮዎችን ለሌሎች ለእርባታ አገልግሎት ከማሠራጨታቸዉ በፊት ቁጥጥር ማድረግና የእርባታ ፈቃድ እንዳላቸዉ ማረጋገጥ፣

ሐ. ከዝርያ ማራቢያና ማባዣ ማዕከላት ካልሆነ በስተቀር የሀገር ዉስጥና በሀገር ዉስጥ የተላመዱ የዉጭ የዶሮ ዝርያዎች ለዘር ከሀገር እንዳይወጡ ቁጥጥር ማድረግ፣

**6.2.3.** የሀገር በቀል የዶሮ ዝርያዎች ብዝሃ-ዘርደህንነት ስለመጠበቅ

በሀገራችን በተለያዩ የግብርና ሥነ-ምህዳሮች ዉስጥ የተለያዩ የሀገር በቀል የዶሮ ዝርያዎች እንደሚገኙ ይታወቃል። የነኚህ ዝርያዎች ብዝሃ-ዘራቸዉን ለሀገሪቱ ትልቅ ሀብት በመሆኑ በመሰብሰብና በመጠበቅ የሀገር በቀል ዶሮዎች ዝርያቸዉና ዘራቸዉ እንዳይጠፉና በሚፈለግበት አገልግሎት ላይ ማዋል ይገባል።

ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል ተብሎ ከዉጭ የሚገቡ የዶሮ ዝርያዎች ወደ ሀገር ውስጥ ማስግባትና ቁጥጥር ባነሰዉ መልኩ ከቦታ ወደ ቦታ ማዘዋወር  እንደዚሁም ከሀገር በቀል ዶሮዎች ጋር ቅጥ ባጣ መልኩ ማሰራጨትና ማዳቀሉ በሀገር በቀል ዶሮዎች ዉስጥ የሚገኘዉ መጠነ ሰፊ የዘረመል ተለያይነት እንዲጠብ ስለሚያደርግ ሀገሪቱ በዘርፉ ያላትን እምቅ የዘረመል ሀብት አደጋ ላይ ሊጥለዉ ይችላል። በተጨማሪም ከዉጭ የገቡ የዶሮ ዝርዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ማዛወር ለበሽታ መዛመት ምክንያት ስለሚሆን ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል። በመሆኑም የሀገሪቱ የዶሮ ብዝሃ-ዘር ለመጠበቅና የተመረጡ የሀገር በቀል የዶሮ ዝርያዎች ለሕብለ-በራኄ መሸርሸርና ለተዛማጅ በሽታ እንዳይጋለጡ የሚከተለዉ የፖሊሲ አቅጣጫ ተቀምጧል።

ፖሊሲ፦ የሀገር በቀል ዶሮዎች ብዝሃ-ዘር እንዲጠበቅና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲዉል እንደዚሁም  የተሻሻሉ የዉጭ ሀገር የዶሮ ዝርያዎች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡም ሆነ በሀገር ዉስጥ ሲዘዋወሩና ለማዳቀል ተግባር ሲዉሉ ቁጥጥር ይደረጋል።

ስትራቴጂ፦

ሀ. የሀገር በቀል የዶሮ ዝርያዎችና ዘሮች ባሉበት አካባቢና ከአካባቢያቸዉ ዉጭ  በመጠበቅ ዝርያቸዉና ዘራቸዉ እንዳይጠፉና ጥቅም ላይ እንዲዉል ማድረግ፣

ለ. የዘረመል ባንክ ተቋቁሞ የሀገር በቀል የዶሮ ዝርያዎችና ዘሮች ብዝሃ-ዘር እንዲጠበቅ ማድረግ፣

ሐ. በየጊዜዉ የሀገር በቀል ዶሮዎች ዝርያዎችና ዘሮች ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ ቆጠራና ምዝገባ ማካሄድ፣

መ. ከዉጭ ሀገር የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች የማስገባቱ ጉዳይ ታማኝነት ካላቸዉና ታዋቂ ከሆኑ የዝርያ ካምፓኒዎች ብቻ ማድረግ

ሠ. ከውጪ አገር ወደ ሀገር ዉስጥ የሚገቡ የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች ወደ ሀገር ዉስጥ ሲገቡ የጤና ቁጥጥር ማድረግ፤

ረ. ከዉጭ የገቡ የዶሮ ዝርያዎች የሀገር በቀል ዶሮዎች ወደሚበዙበት ወደ ገጠሪቱ ማህበረሰብ የሚደረግ ዝዉዉር መቀነስ

ሰ. የዉጭ ሀገር ዶሮዎች በሀገር ዉስጥ ከሀገር በቀል ዶሮዎች ጋር ለማዳቀል ሲታሰብ አስፈላጊዉ ጥንቃቄ ማድረግ

ሸ. የዉጭ ዝርያዎች በገጠሪቱ ክፍል ማርባት ወይም ለማዳቀል ተግባር መጠቀም ሲያስፈልግ የእርባታዉ ቦታ በሽቦ አጥር በመከለል ያልተፈለገ የዘረመል መበረዝ እንዳይኖር መቆጣጠር

**6.2.4.** በዶሮ ሀብት ልማትና ምርምር ዘርፍ የባዮቴክኖሎጂ ዘዴዎች መጠቀም

ባዮቴክኖሎጂ የሀገር በቀል ዶሮዎች ልዩነታቸዉን ለማጥናት፣ ዝርያዎችን ለማፍለቅ፣ ለማሻሻልናለመጠበቅ ሊሰጠዉ የሚችለዉ ጥቅም እጅግ ከፍተኛ ነዉ። ነገር ግን በሀገራችን በየትኛዉምየእንስሳት ዕርባታ ዘርፍ ባዮቴክኖሎጂን በተለይ የዘረመል ቴክኖሎጂዎች በተግባር እየተጠቀምንአይደለም። ስለዚህ የሀገራችን የዶሮ ሀብት ልማት በባዮቴክኖሎጂ ለመደገፍ ምቹ ሁኔታዎችለመፍጠር የሚከተለዉ የፖሊሲ አቅጣጫ ተቀምጧል።

ፖሊሲ፡- በሀገሪቱ የሚተገበሩ የዝርያ ማፍለቅ፣ ማላመድ፣ ማሻሻልና መጠበቅ የምርምር ሥራዎች በባዮቴክኖሎጂ ዘዴዎች እንዲደገፉ ይደረጋል

ስትራቴጂዎች፡-

ሀ. ባዮቴክኖሎጂ ለዝርያ ማፍለቅ፣ ማላመድ፣ ማሻሻልና መጠበቅ ሥራዎች ሊኖረዉ የሚችለዉ ጥቅም አስመልክቶ ለተለያዩ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች መስጠት፣

ለ. በአጭርና በረጅም ጊዜ ስልጠናዎች በመታገዝ በሀገራችን በእንስሳት ባዮቴክኖሎጂ በቂ እዉቀት ያለዉ የሰዉ ኃይል በብዛት ማፍራት፣

ሐ. ባዮቴክኖሎጂን ለዝርያ ማፍለቅ፣ ማላመድ፣ ማሻሻልና መጠበቅ ሥራዎች ለመጠቀም ስታንዳርድ ፕሮቶኮሎች እንዲዘጋጁ ማድረግ፣

መ. ለባዮቴክኖሎጂ ሥራዎች የሀገር ዉስጥ የላቦራቶሪ አቅም መገንባትና የሚያስፈልጉ የላቦራቶሪ ግብዓቶች በቀላሉ የሚገኙበት ስርዓት መዘርጋት፣

ሠ. በባዮቴክኖሎጂ ዘርፍ ምርምርና ልማት ከሚያካሄዱ ከሀገር ዉስጥና ከዉጭ ተቋማት ጋር በቅንጅት መሥራት

**6.2.5.** የዶሮ ዝርያ ማባዛትና ማሰራጨት

በሀገራችን የዶሮ ልማት ዉጤታማ ለማድረግ እንደማነቆ ከሆኑ ችግሮች አንዱ የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች ለተጠቃሚዉ ህብረተሰብ በሚፈለገዉ መጠንና ጊዜ በቀጣይነት ማድረስ አለመቻል ነዉ። ለዚህም አስተዋፅዖ ሊያደርጉ ከሚችሉ ጉዳዮች አንዱ የዘመነ የዝርያ ስርጭት ሥርዓት አለመኖር ነዉ። ከዚህም በተጨማሪ በምርምር የፈለቁ ወይም በማላመድ የተገኙ ዝርያዎች የማሻሻያና በበቂ መጠን አባዝቶ ለተጠቃሚዉ ህብረተሰብ ቀጣይነት ባለዉ መልኩ ለማቅረብ የማባዣ ማዕከላት በቁጥር አናሳ መሆንና ያሉት ጥቂት የሚባሉ የማባዣ ማዕከላትም በብዛት ዝርያዎችን የማባዛት አቅማቸዉ ዉስን መሆኑ ነዉ። ስለዚህ በሀገራችን የዶሮ

ልማት እንዲስፋፋ ብቃት ያላቸዉ ዝርያ ማሻሻያና ማባዥያ ማዕከላት መፍጠር ያስፈልጋል። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚያግዙ የፖሊሲ አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተቀምጠዋል።

ፖሊሲ፡- በሀገሪቱ ለተለያዩ የዶሮ ዕርባታ ዘዴዎች የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች አቅርቦት እንዲኖር ይደረጋል።

ስትራቴጂዎች፡-

ሀ. ለጭሮሽ ዕርባታ ዘዴ የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች አቅርቦት ቀጣይነት እንዲኖር ለማድረግ በአገር ውስጥ በመረጣ የተሻሻሉ ወይም በማዳቀል (እስከ 50 ፐርሰንት የደም መጠን) የተገኙ ጥምር ጠቀሜታ ያላቸዉ ዝርያዎች በየክልሉ በሚገኙ የዶሮ ማባዣ ጣቢያዎች በበቂ ሁኔታ በማባዛት የአንድ ቀን ዕድሜ ያላቸዉን ጫጩቶች እስከ 45-60 ቀን እድሜ በማሳደግ ለተጠቃሚዉ ህብረተሰብ ይሰራጫሉ፣

ለ. በተሻሻለ የቤተሰብ ዕርባታ ዘዴ ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ ጥምር ጠቀሚታ ያላቸዉ የዶሮ ዝርያዎች አቅርቦት ቀጣይነት እንዲኖር ለማድረግ በሀገር ዉስጥ በመረጣ የተሻሻሉ ወይም በማላመድ የተገኙ ወይም በማዳቀል የመነጩ ሴንቴቲክ ዝርያዎች በየክልሉ በሚገኙ የዶሮ ማባዣ ጣቢያዎች በበቂ ሁኔታ በማባዛትና የአንድ ቀን ዕድሜ ያላቸዉ ጫጩቶች ከ45 - 60 ቀን እድሜ በማሳደግ ለተጠቃሚዉ ህብረተሰብ ይሰራጫሉ፣

ሐ. በስፔሻላይዝድ ዕርባታ ዘዴ ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ የዶሮ ዝርያዎች አቅርቦት ቀጣይነት እንዲኖር ለማድረግ 1ኛ) መስራችና ቅድመ መስራች የእንቁላል ወይም የሥጋ ዝርያዎች በቀጥታ ከዉጭ በማስገባት በመንግስትና በግል ዕርባታዎች በማባዛት ወደ ተጠቃሚዉ ህብረተሰብማሰራጨት፣ 2ኛ) ከዉጭ ከገቡት ዝርያዎች በማዳቀል ሴንቴቲክ ዝርያ ማመንጨትና አባዝቶ ለተጠቃሚ ማሰራጨት፣ 3ኛ) ከዉጭ ሀገር የዝርያ ባለቤት ካምፓኒዎች በሀገር ዉስጥ መጥተዉ በዝርያ አቅርቦት ላይ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ማድረግ፣

ፖሊሲ፡- በሀገር ዉስጥ በምርምር የፈለቁ ወይም በማላመድ የተገኙ የዶሮ ዝርያዎችን የሚያሻሽሉና በብዛትና በጥራት የሚያባዙ ነባር ማዕከላት ይጠናከራሉ፤ አዳዲስ ማእከላትም ይቋቋማሉ።

ስትራቴጂዎች፡-

ሀ. በሀገሪቱ የሚገኙ የነባር የዶሮ ዝርያ ማሻሻያና ማባዥያ ማዕከላት ማስፋፋትና መጠገን

ለ. የዝርያ ማሻሻያና የማባዥ ማዕከላት ዕጥረት ያሉባቸዉ የሀገሪቱ ክፍሎች በመለየት ለአዳዲስ ማዕከላት መገንቢያ የሚሆኑ ቦታዎች መለየት

ሐ. በተለዩ ቦታዎች ስታንዳርዳቸዉ የጠበቁ አዳዲስ የዝርያ ማሻሻያና የማባዣ ማዕከላት ማቋቋም

መ. አዳዲስ የዝርያ ማሻሻያና የማባዣ ተቋማት በመገንባትና ነባር ማዕከላት በመጠገን ላይ ባተኮሩ የልማት ሥራዎች ቅድሚያ ለባለሀብቶች፣ ማህበራት፣ ግብር-ሰናይ ድርጅቶች በመስጠት የመንግስት ተቋማትን ተሳትፎም ማሳደግ

ሠ. የዶሮ ማሻሻያና ማባዥያ ማዕከላት በመሥራት ለሌሎች ለማከራየትም ሆነ በግል ለብዜት ሥራ ለመጠቀም ብለዉ በዘርፉ ለሚሰማሩ አካላት የብድርና የመሬት አቅርቦት ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ

**6.2.6.** ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸዉ የአዕዋፍ ዝርያዎች ስለመለየትና መጠቀም

ሀገራችን በዉል ተለይተዉ ያልታወቁ ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸዉ የአዕዋፍ ዝርያዎች ባለቤት ስትሆን ከነዚህም ዉስጥ ሰጎን፣ ዳክዬ፣ ጅግራ፣ የጊኒ ወፍ እና ሌሎች ዝርያዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ። ሆኖም እነዚህ የአዕዋፍ ዝርያዎች ከሚሰጡት ጠቀሜታ አንፃር አስፈላጊዉ ትኩረት ባለመሰጠቱ ዝርያቸዉ፣ ስርጭታቸዉ፣ ምርታማነታቸዉና ብዛታቸዉ በዉል ተለይተዉ አይታወቅም፡

በአሁኑ ወቅት የእነዚህ የአዕዋፍ ዝርያ ዉጤቶች በዓለም ገበያ ላይ ተፈላጊና ከፍተኛ ዋጋ እያስገኘ የመጣ በመሆኑ ለልማቱ ትኩረት ተሰጥቶ ሀገሪቷ ከእነዚህ ዝርያዎች ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ መደረግ ይኖርበታል። ይህ ለማድረግ የሚያስችል የሚከተለዉ የፖሊሲ አቅጣጫ ማስቀመጥ አስፈልጓል።

ፖሊሲ፡- በሀገር ዉስጥ የሚገኙ እንደ ሰጎን፣ ዳክዬ፣ ጅግራ እና የጊኒ ወፍ  የማሰሉት ዝርያዎች ብዛታቸዉ፣ ስርጭታቸዉና ምርታማነታቸዉ ተጠንተዉ እንዲለዩና ተስማሚ በሆኑ አከባቢዎች በማላመድና በማባዛት ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ይደረጋል፡

ስትራቴጂዎች፡-

ሀ. በሀገር ዉስጥ የሚገኙ የሰጎን፣ ዳክዬ፣ ጅግራ እና የጊኒ ወፍዝርያዎች ስርጭታቸዉ፣ ምርታማነታቸዉና ብዛታቸዉ በጥናት መለየት፣

ለ. በቀላሉ የመላመድ ባህሪ ያላቸዉ የሰጎን፣ ዳክዬ፣ ጅግራ እና የጊኒ ወፍ ዝርያዎች መምረጥ፣ ማሻሻል፣ ማራባትና ማሰረጨት፣

ሐ. እነዚህ የአዕዋፍ ዝርያዎች ለሀገሪቱ የሚያስገኙት የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ህብረተሰቡ በመገንዘብ በልማቱ ሥራ ላይ እነዲሳተፍ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣

**6.2.7.** የዶሮ ዝርያና ዘር ጥራትና ደረጃን ስለማዉጣትና መቆጣጠር

በምርምር የሚፈልቁ ወይም በማላመድ የሚገኙ የዶሮ ዝርያና ዘር ደረጃዉ የጠበቀ የጥራት ደረጃ ሊኖራቸዉ ይገባል። የዝርያና የዘር ጥራትና ደረጃ በአሠራር፣ በአያያዝ ጉድለትና በሌሎች ምክንያቶች ዝቅተኛ ሊሆን ስለሚችል የሚሰራጨዉ የዶሮ ዝርያ ወይም ዘር የሚያስገኘዉ ዉጤትም አነስተኛ ይሆናል። በሀገራችን የዶሮ ዝርያና ዘር የጥራትና ደረጃን አስመልክቶ ጎልቶ የወጣና በሥራ ላይ የዋለ አሠራር ብዙም አይታይም። ስለዚህ የዶሮ ዝርያዎችና ዘሮች ርቢ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሁሉ ጥራትና ደረጃቸዉን የጠበቁ ዝርያዎችና ዘሮች ለተጠቃሚዎች እንዲያቀርቡ የሚከተለዉ የፖሊሲ አቅጣጫ ተቀምጧል።

ፖሊሲ፦ በሀገራችን ለዶሮ ዝርያና ዘር የጥራትና ደረጃ መስፈርቶች ይኖሯታል።

ስትራቴጂዎች፦

ሀ. ለዶሮ ዝርያና ዘር ጥራት መገምገሚያ መስፈርቶችን የያዘ ፕሮቶኮል ማዘጋጀት

ለ. የዶሮ ዝርያዎችና ዘሮች በመስፈርቱ መሠረት ጥራትና ደረጃቸዉን መገምገም፣

ሐ. የዶሮ ዝርያና ዘር ጥራትና ደረጃ በተግባር መተግበሩ መከታተልና መቆጣጠር፣

### **6.2.8.** የዶሮ ዝርያ፣ ምርትና ምርታማነት ነክ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ስለመዘርጋት

በዶሮ ዕርባታ ዉስጥ ምርትና ምርታማነት እንደዚሁም የዘር ሐረግ ገላጭ የሆኑ መረጃዎች መያዝ ለዝርያ መረጣና ምርትና ምርታማነት ለማሻሻል እጅግ ጠቃሚ ነዉ። ነገር ግን በሀራችን በዶሮ ዕርባታም ሆነ በሌሎቸ የእንስሳት ዕርባታዎች ዉስጥ መረጃ በዘላቂነት የመያዝና የመጠቀም ልምድ እጅግ አናሳ ነዉ። ስለዚህ በቀጣይ ማዕከላዊነቱን የጠበቀና ወጥነት ያለዉ የዶሮ ዘር ሀረግ፣ ምርትና ምርታማነት ገላጭ የሆነ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ የሚከተለዉ የፖሊሲ አቅጣጫ ተመላክቷል።

ፖሊሲ፦ በሀገሪቱ የዶሮ ዕርባታን አስመልክቶ ብሔራዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ይዘረጋል።

ስትራቴጂዎች፦

ሀ. የብሔራዊ መረጃ ማሰባሰቢያ፣ መተንተኛ እና ማሰራጫ ሥራዎችን ማዕከላዊ ማድረግ፣

ለ. ወጥነት ያለዉ የዶሮ ርቢ ሥርዓትን የሚያግዝ የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት፣

ሐ. በሀገሪቱ በመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች መስጠት፣

**6.3.** የዶሮ መኖ አቅርቦት

የዶሮ መኖ በዘመናዊ የዶሮ እርባታ ስርዓት ከአጠቃላይ የእርባታ ወጪ ከ 60 - 70 በመቶ በላይ የሚሆነውን ድርሻ እንደሚሸፍን ይገመታል። ለሀገራችን የዶሮ እርባታው ዘርፍ እድገት ማነቆ ከሆኑ በርካታ ችግሮች መካከል የዶሮ መኖ በጥራት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ እና በሚፈለገው መጠን ቀጣይነት ባለው መልኩ ማቅረብ አለመቻል በዋነኛነት ተጠቃሽ ነው።

በተለይ በዶሮ መኖ ቅንብር ሂደት ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው የሚገኙት በቆሎ (በተለይም ቢጫ በቆሎ) እና አኩሪ አተር ለዶሮ መኖ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ዓላማ አድርገው እንዲያመርቱ ተለይተው በመንግስትም ሆነ በግል ባለሀብቶች የተቋቋሙ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች ባለመኖራቸው በዶሮ መኖ ማቀነባበር የተሰማሩ የመንግስትም ሆነ የግል ባለሀብቶች እነዚህን ግብዓቶች የሚያገኙት ለሰው ምግብነት ፍጆታ ተብሎ ከሚመረተው ምርት በመሻማት መሆኑ ይታወቃል። ይሁንና ዘርፉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመጣ ቁጥር የእነዚህን ግብዓቶች ፍላጎት እንደዚሁ በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚጨምርና ይህንንም ፍላጎት ለማሟላት በምግብ እህል አቅርቦት ላይ የተመሰረተ መሆኑንና ከዚህም ጋር ተያይዞ በሚፈጠረው የአቅርቦት እጥረት የእነዚህ ጥሬ ዕቃዎች ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄድ ላይ ይገኛል። ለዚህም ቀጥተኛ ማስረጃ የሚሆነው የተቀነባበረ መኖ መሸጫ ዋጋ ከምን ጊዜውም በላይ እየጨመረ መሄድ ሲሆን ከዚህም ጋር ተያይዞ የዶሮ ውጤቶች ዋጋ እንደዚሁ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጨመር ላይ ይገኛል።

በመሆኑም ከዶሮ መኖ አቅርቦት ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታትና ከዘርፉ የሚጠበቀውን ምርትና ምርታማነት በማሻሻል ዘርፉ ሊያበረክት የሚችለውን ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማሳደግ እንዲቻል ከዚህ በመቀጠል ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራባቸው የሚሹ ጉዳዮችና የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተመላክተዋል።

**ፖሊሲ፡-** በዶሮ መኖ ቅንብር ውስጥ በብዛት የሚካተቱት የመኖ ጥሬ ዕቃዎች ቢጫ በቆሎና አኩሪ አተር በስፋት እንዲመረቱ ይደረጋል።

ስትራቴጂዎች፡-

ሀ. ለቢጫ በቆሎና አኩሪ አተር ማምረቻ የሚውሉ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች በመለየት ለዚሁ ተግባር እንዲውሉ ማድረግ፣

ለ. በቢጫ በቆሎና አኩሪ አተር ልማት ላይ ሊሳተፉ የሚችሉ ባለሀብቶች መጋበዝ፣ አስፈላጊውን ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር እና ድጋፍ ማድረግ፣

ሐ. ሴቶችና ወጣቶች እንዲደራጁ በማድረግ በቢጫ በቆሎና አኩሪ አተር ልማት ላይ እንዲሳተፉ የብድር አቅርቦትና ሌሎች ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር፣

መ. ለቢጫ በቆሎና አኩሪ አተር ልማት እንዲውሉ የተዘጋጁ መሬቶች ለታለመው ዓላማ

መዋላቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ፣

ሠ. ቢጫ በቆሎና አኩሪ አተር የሚያመርቱ አርሶ አደሮችን ማበረታታት እንዲሁም ምርታቸውን ከገበያ ጋር ማስተሳሰር

ረ. ለዘይት/ስታርች ፕሮሰሲንግ ኢንደስትሪዎች ማበረታቻ የሚሰጥበትና ተረፈምርቱ በዝተኛ ዋጋ የሚቀርብበን ሁኔታ ማመቻቸት

**ፖሊሲ፡- የዶሮ መኖ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ይቋቋማሉ።**

ስትራቴጂዎች፡-

- ✔ በዶሮ መኖ ማቀነባበር ለሚሳተፉ ባለሀብቶች የመሬት አቅርቦት፣ የመኖ ማቀነባበሪያ መሳሪያዎች ከቀረጥ ነጻ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታና እና የብድር አቅርቦት ማመቻቸት፣
- ✔ የዶሮ መኖ ማቀነባበሪያ መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲፈበረኩ ማድረግ፣

**ፖሊሲ፡- የመኖ ጥራትና ደህንነት የሚያስጠብቁ ደረጃዎች ይወጣል፤ጠንካራ የዶሮ መኖ ጥራት ፍተሻ ስረዓት ይዘረጋል።**

ስትራቴጂዎች፡-

- ✔ የተጠናከረ የዶሮ መኖ የጥራት ደረጃ ቁጥጥርና ክትትል ስርዓት መዘርጋት፤
- ✔ ለጥራት ደረጃ የተጠናከረ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓት እንዲኖር ማድረግ፣
- ✔ የዶሮ መኖ የዶሮ አርቢውን የመግዛት አቅምና ተደራሽነት ባማከለ መልኩ በአግባቡ ታሽጎና የምርት መግለጫ ይዞ እንዲቀርብ ማድረግ፣
- ✔ በዘመናዊ መሳሪያዎችና በሰለጠነ የሰው ሀይል የተደራጁ የመኖ ይዘትና ጥራት ምርመራ የሚያካሄዱ ላበራቶሪዎች ማቋቋም፣

**ፖሊሲ፡- ከውጭ በውድ ዋጋ የሚገቡ የመኖ ጥሬ ዕቃዎች (ፕሪሚክስ) በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ይደረጋል።**

ስትራቴጂዎች፡-

- ✔ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡና በሀገር ውስጥ ሊመረቱ የሚችሉ የመኖ ጥሬ ዕቃዎች መለየት፣

- ✔ በዚህ ዘርፍ መሰማራት ለሚፈልጉ የግል ባለሀብቶች አስፈላጊውን የመሬትና የብድር አቅርቦት ማመቻቸት፣

ፖሊሲ፡- ለጭሮሽ፣ ለባህላዊና ለተሻሻለ የቤተሰብ ዶሮ እርባታ ስርዓት የሚውል የድጎማ መኖ አቅርቦት ፓኬጅ እንዲዘጋጅ ይደረጋል።

ስትራቴጂዎች፡-

- ✔ በተያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የግብርና ስነ-ምህዳር ቀጠናዎችና ወቀቶችን መሰረት ባደረገ መልኩ ለባህላዊና ለተሻሻለ የቤተሰብ ዶሮ እርባታ ስርዓት ለጭሮሽ ሊውሉ ሊገኙ የሚችሉ የመኖ ጥሬ እቃዎች ምንጮችና አቅርቦትና ይዘት መለየት፣
- ✔ በየአካባቢው የሚገኝ የመኖ ጥሬ እቃ በመጠቀም መሰረት ወቅቱንና የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት ያደረገ የድጎማ መኖ ቅንብር ቀመር ማዘጋጀት፣

## 6.4. የዶሮ ጤና

በሀገራችን በተለያዩ ስነምህዳር ሊረቡ የሚችሉ የዶሮ ሀብት ያላት ሲሆን በተለያዩ የዶሮ በሽታዎች መስፋፋት ምክንያት ከዘርፉ ተገቢውን ጥቅም እያገኘች እንዳልሆነ ይታመናል።በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያሳዩት አብዛኛውን አገሪቱ ሽፍኖ ከሚገኘው የባህላዊና የተሸሻለ የቤተሰብ ዶሮ እርባታ ስርዓት በየዓመቱ ከአጠቃላይ የዶሮ ቁጥር በአማካኝ እስከ 50 በመቶ የሚደርስ ሞት ይከሰታል፤እንደዚሁም በአነስተኛና መካከለኛ እስፔሻላይዝድ የዶሮ እርባታ ውስጥ ቁጥሩ ቀላል የማይባል የዶሮዎች ሞት ይከሰታል። የበሽታዎች በስፋት መኖርና ተመጣጣኝ የሆነ ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ የዶሮ ጤና ሥርዓት አለመዘርጋት ተገቢውን ድርሻ እንዳናገኝ ያደረገን ሲሆን፣ አንዳንድ በሽታዎች ወደ ሰው የሚተላለፉ በመሆናቸው በህዝብ ጤና ላይም የሚያደረሱት ተፅኖም ከፍተኛ ነው። በመሆኑም ሀገራችን ከዶሮ ሃብት ልማት ማግኘት ያለበትን ጥቅም ለማግኘት የዶሮ ጤና አጠባባቅ ስርዓትን መዘርጋት ፣ በሽታዎችን የመቆጣጠሪና የመከላከያ ዘዴዎችን በዘመናዊም ሆነ በባህላዊ የዶሮ አረባብ ተግባራዊ ማድረግ፣ እንዲሁም የዶሮ ጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተደራሽነት እና ሌሎች ከጤና ጋር ተያያዥ የሆኑ ስራዎችን መስራት አስፈላጊ ነው።

### 6.4.1. የዶሮ በሽታ ሰርቪላንስ እና የበሽታ ሪፖርት ስርዓቱን ስለማጠናከር

ፖሊሲ ፡ በሀገራችን የዶሮ የሰርቪላንስ እና የበሽታ ሪፖርት ስርዓቱ ይጠናከራል፤እንዲዘምንም ይደረጋል።

ስትራቴጂዎች፡-

- በሀገራችን የተጠናከረ የዶሮ በሽታ አሰሳና ቅኝት ማድረግ፣

- በአገራችን ያለውን የዶሮ በሽታ ስርጭት በዝርዝር መለየትና የስጋት ደረጃውን ማወቅ፣
- የዶሮ በሽታዎች መረጃ አያያዝና ሪፖርት አደራረግ ላይ የባለሙያዎችን አቅም ማጎልበትና የመረጃ ስርዓቱን ማጠናከር፣
- የዶሮ በሽታ መከላከል፣ቁጥጥርና ሰርቪላንስ ቡድን ማቋቋም

**6.4.2.** የዶሮ ጤና መከላከልና ቁጥጥር ስርዓት ስለመሻሻል

የተለያዩ የዶሮ በሽታዎች በሀገራችን ሪፖርት የተደረጉ እና የሚገኙ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ በርካታ በሽታዎች ከዶሮ ጤና እንክብካቤ አያያዝና አመጋገብ ጉድለት በመነጨ የሚከሰቱ በሽታዎች በስፋት ይገኛሉ ። በዚሁ መሠረት የዶሮ ሀብት ልማት ዘርፍን ለማሳደግ በዶሮ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር እና በሌሎች በዶሮ ጤና አጠባበቅ ላይ መስራት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ፖሊሲ - በሀገራችን በዶሮ ሀብት ልማት ዘርፍ የበሽታ ቁጥጥር ስርዓትይጠናከራል፤

ስትራቴጂዎች፡-

- ሥነ ህይወታዊ ደህንነት (ባዮ ሴክዩሪቲ) ቁጥጥር ስርዓት በየእርባታ ዓይነቱ ማዘጋጀትና እንዲተገበር ክትትልና ድጋፍ ማድረግና የብቃት ማረጋገጫ (ሰርቲፊኬሽን) ስርዓት መዘርጋት
- በሰርቪላንስ መረጃው ላይ በመመስረት በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች  ለተለዩ ለዋና ዋና የዶሮ በሽታዎች የመከላከልና ቁጥጥር ስትራቴጂ ማዘጋጀት እና ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣ውጤታማነቱን መከታተል
- የማህበረሰብ አቀፍ የዶሮ በሽታ ክትባት ስርዓት መዘርጋት ፤ ለተገባራዊነቱም ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- የፌደራልና የክልል ቀጥተኛ የስራ ግንኙነት እንዲኖርና እንዲጠናከር ማድረግ
- በዶሮ በሽታ መቆጣጠርና መከላከል ስራ ላይ በግል የተመዘገቡ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ተሳትፎን ለማሳደግ አመቺ ሁኔታን መፍጠር
- የዶሮ ጤና የትምህርት ስርዓት አሰጣጥን ማሻሻልና ተከታታይ ትምህርት መስጠት
- የመንግስትና የግል የእንስሳት ጤና ክሊኒክና ኬላ በበሽታ መከላከልና ቁጥጥር እንዲሁምበሌሎች የዶሮ ጤና አገልግሎቶች እንዲጠናከሩ ማድረግ
- ከፍተኛ ስጋት ለሆኑ የዶሮ በሽታዎችየአደጋ ጊዜ ዝግጁነትና ምላሽ እስትራቴጂ /ማዘጋጀት፣
- ለበሽታ መከላከልና ቁጥጥር የሚያስፈልጉ የህግ ማዕቀፎችን በመፈተሽ ማሻሻልና ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ

**6.4.3.** የዶሮ ክትባት፣ መድሀኒትና የህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት ስለማሻሻል

በሀገራችን ክትባት ፣መድሃኒትና የህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት እጥረት እንዳለና በተለይ መድሃኒትና የህክምና መሳሪያዎች አብዛኞቹ ከውጪ እንደሚገቡ ይታወቃል።ይህም የአቅርቦት ውስንነት እየፈጠረና የውጪ ምንዛሪ እየጠየቀ በመሆኑ በቀጣይ በሀገር ውስጥ እንዲመረት ማበረታታትና የግል ዘርፍን ማሳተፍ ያስፈልጋል ።

ፖሊሲ፡የዶሮ ክትባት፣ መድሃኒት፣ የላብራቶሪ መሳሪያዎችና ኬሚካሎች እንዲሁም የህክምናመሳሪያዎች ግብአት አቅርቦት እንዲሻሻል ማድረግ፤ በሀገር ዉስጥም ማምረት

ስትራቴጂዎች፡

- በሀገር ውስጥ በክትባት፣ መድሃኒት እና የህክምና መሳሪያዎች ማምረት ላይ የግል ባላሀብቱ እንዲሳተፉ ድጋፍ ማድረግ ፣
- በሀገር ውስጥ ያለውን አቅርቦት ለማሳደግ የቡብሔራዊ ጤና ጥበቃ ኢንስቲቲውትን አቅም ማሳደግ፣
- ባለሀብቶችና ማህበራት የዶሮ ጤና ጥበቃ የሚውሉ ግብዓቶችን እንዲያስገቡና እንዲያስራጩ ማመቻቸት ፣
- በሀገራችን የክትባት አቅርቦትን ተደራሽ ለማድረግ በየክልሉ የክትባት ማቀዝቀዣ ዲፖዎችን መገንባት ለላብራቶሪዎች የሚያገለግሉ ማሳሪያዎች፣ ኪቶች ፣ኬሚካሎች፣ ሪኤጀንቶችና ሌሎች አስፈላጊ ግብአቶች አቅርቦት ማሳደግ

### 6.4.4 የዶሮ ክትባትና መድሀኒት ጥራት ስለማሻሻልና ስለመቆጣጠር

የዶሮ ክትባት፣መድሃኒትና የዶሮ ሕክምና መሣሪያዎች ጥራታቸዉ፣ ፈዋሽነታቸዉንና ደህንነታቸዉን በተላያዩ ምክንያቶች ሊያጡና ሊለወጡ ይችላሉ። ስለዚህ እነዚህ የዶሮ ክትባትና መድሃኒት ፈዋሽነታቸው የተረገገጠ መሆን አለባቸው። በተጨማሪምበሰዉና በዶሮ ሕይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርሱ ስለሚችሉ ከጥሬ ዕቃ ዝግጅት ጀምሮ በአመራረት፣ በክምችት አያያዝ፣ በማስመጣት፣ በማከፋፈልና በሚላክበት ወቅት አስፈላጊዉ ጥንቃቄና ክትትል መደረግ አለበት።ይህንንም ማሻሻል እና መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ፖሊሲ፦ ጥራቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠየዶሮ ክትባትናመድሃኒት ላይ እና የህክምና መሳሪያዎች ላይ የቁጥጥር ስርዓቱ ይጠናከራል

ስትራቴጂዎች፡

- ከውጭ የሚገቡና በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የዶሮ ክትባት በዶሮ በሽታዎች ሴሮታይፕ ጥናት ላይ መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- በሀገራችን የሚመረቱ የዶሮ ክትባቶች በዓይነትና በብዛት እንዲሁም የጥራት ደረጃቸው የተጠበቀ እንዲሆን ከተለያዩ ተቋማት ጋር በቅርበት መስራት፣
- በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የዶሮ ክትባቶችና መድሃኒቶች ዓይነትና ጥራት ላይቁጥጥር ማድረግ
- ከውጭ ሀገር ለሚገቡ ለዶሮ የህክምና መሳሪያዎች ዓይነት፣ጥራትና መጠን ላይቁጥጥርበማድረግእንዲገቡና በጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ፣

- ከዉጭ የሚገቡ የዶሮ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የኳራንቲን ቁጥጥር ሥርዓትና የኳራንቲን መሠረተ ልማቶች እንዲጠናከሩና እንደዲስፋፉ ማድረግ፣
- የህገ ወጥመድኃኒትና ክትባት ዝውውር ላይ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት እንዲኖር ማድረግ፣

**2.** የደሮ በሽታን ዕውቀትና የመመርመር አቅም ማሳደግ

በሀገራችን እያደገ የመጣውን የደሮ ኢንደስትሪ እየተፈታተነው ያለው በሽታ በመሆኑ ይህንን ችግር ለመፍታት የምርመራአቅማችንን ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ፖሊሲ ፦ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ላብራቶሪዎችንና በዘርፉ የየደረጃው የሚገኘውን ሙያተኛ የመመርመር አቅም ማጎልበትና ማስፋፋት

ስትራቴጂዎች፡

- በሽበታ እንስሳት ጤና ላብራቶር የደሮ ጤና ኤክስፐርቶች ስብስብ ማቋቋም አቅም መገንባት እና በደሮ በሽታ ዙሪያ ከፍተኛው የምርመራና እርምጃ አወሳሰድ ውሳኔ ሰጭ አካል እንዲሆን ማድረግ
- የደሮ ልማት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች የሚገኙየክልል የእንስሳት ጤና ላብራቶሪዎች የደሮ በሽታዎች ምርመራ አቅም በሰው ኃይልና በመሳሪያ እንዲያጎለብቱ ማድረግ ፣
- እንስሳት ጤና ሙያተኞችን በበሽታ ልየታ፣ ናሙና አወሳሰድና አላላክ ላይ አቅማቸው እንዲጎለብት ማድረግ ፣
- የተለያዩ የመረጃ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም በየደረጃው በሚገኙ ላብራቶሪዎች መካከል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋት ፣

### 6.4.5 የዶሮ ሙብት (animal Welfare) ጥበቃ ስለመተግበር

ዶሮዎች እንደማንኛውም እንስሳት ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን የእንስሳት ደህንንት (animal Welfare) ሙብቶች (ከመራብ ፣ ከመጠማት፣ ከመጨናነቅ ፣ የተመጣጠነ መኖ የማግኘት እንዲሁም ከአደጋና ከበሽታ እና ከመረበሽ) ነጻ የመሆን ሙብት ያላቸው መሆኑ ቢታወቅም በአብዛኞቹ የዶሮ አርቢዎች እና በማህበረሰቡ ሲተገበር አይገኝም።ይህም ኋላቀር የአያያዝ ስርዓት አሁን ላለው የዶሮ ምርትና ምርታማነት አነስተኛ መሆን እንደ ምክንያት ይጠቀሳል።በመሆኑም የዶሮዎችን ደህንነት በመጠበቅ ምርትና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የዶሮዎችን ደህንነት ጥበቃ መተግበርና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ፖሊሲ፦የዶሮ ደህንነት **(Poultry Welfare)** እንዲጠበቅይደረጋል

ስትራቴጂዎች፡

- ዶሮዎች እንደማንኛውም እንስሳት ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ህብረተሰቡን ወይም ዶሮ አርቢ አካላትን የእንስሳት ደህንነት መርሆችን በመከተል የዶሮ ደህንነት ላይ ሰፊ የግንዘቤ ማስጨበጫ ትምህርት በመስጠት እንዲሻሻል ማድረግ ፣ መከታተል፣

- የዶሮእንክብካቤና አያያዝ ደረጃዉን በጠበቀ መልኩ እንዲተገበር ለማስቻል የህግ ማዕቀፎችን አዘጋጅተው በማጸደቅ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ

**6.5.** ምርት ማቀነባበር ሂደት

የዶሮ ምርት ማቀነባበር ሂደትን በተመለከተ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅሞ ምርቶችን ከማቀነባበር አኳያ ገና በጅምር ላይ ያለ ከመሆኑ አንጻር በሀገር ውስጥ ተቀነባብረው ለህብረተሰቡ በምግብነት አገልግሎት የሚውሉ የዶሮ ምርቶች ከቅድመ እርድ እስከ እሴት ጭማሪ ሂደቶች ድረስ ቀላል የማይባል ችግሮች ያሉበት ሲሆን በዋነኛነት ደረጃቸውን የጠበቁ የዶሮ ውጤቶች ማዘጋጃና ማደራጃ ድርጅቶች አለመስፋፋት፤የዶሮ ውጤት ማቀነባበሪያ፣ ማሸጊያ፣ ማከማቻና ማጓጓዣ ቴክኖሎጂ አቅርቦት ውስንነት፤አማራጭ የአመጋገብ ሥርዓትን ለማስፈን የዶሮ ምርቶችን በቀላሉ አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች አለመኖር ፤በምርት አጠቃቀም ላይ የህብረተሰቡ ግንዛቤ ውስንነትና ምርቱን የቅዝቀዜ ሰንሰለቱን ጠብቆ በቀጥታ ለሆቴሎችና ሱፐር ማርኬቶች ለማቅረብ የሚደረግ ጥረት እንዳለ ሆኖ በተቃራኒው ምርቱ በህገወጥ መልኩም እየተመረተና በትራንስፖርት መኪኖች ጥራቱንና ጤንነቱ ባልተጠበቀ መልኩ ለተጠቃሚው በስፋት እየቀረበ ያለ ሲሆን የተጠቃሚውን ፍላጎት በአገር ውስጥ በሚመረቱ የዶሮ ምርቶች ለማሟሟላት ባለመቻሉና ምርትን በሚፈለገው ብዛትና ጥራት ባለመቅረቡ ምክንያት የዶሮ ስጋ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ እየተደረገ ይገኛል። በመሆኑም ችግሮቹን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል የፖሊሲ ጉዳዮችና የአፈጻጸም ስልቶች እንደሚከተለው ቀርቧል።

ፖሊሲ:-ደረጃቸውን የጠበቁ የዶሮ ምርት ማዘጋጃና ማደራጃ ድርጅቶች በግለሰብና በማህበራትእንዲስፋፉ ይደረጋል

ስትራቴጂዎች

- ዘመናዊ የሆኑ የዶሮ ስጋ ማምረቻ፣ የእንቁላል ማቀነባበሪያእና ሌሎች የዶሮ ውጤቶችማቀነባበሪያ ቴክኖሎጂዎችን ከማምረት እስከ መጓጓዝ ቀጥሎ እስከ ማከማቸትና ማስቀመጥ የሚጠይቀውን ቴክኖሎጂ ይዘው ወደስራ ለሚገቡና በእሴት ጭማሪ ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በመንግስት በኩል የተለያዩ ማበረታቻዎች በተለየ መልኩ እንዲፈቀድ ማድረግ (የታክስ እፎይታ፤ የረዝም ግዜ ብድርና የመሰረተ ልማት አቅርቦት፤ማሽነሪዎችን ከቀረጥ ነጻ የማስገባት.......)

- በታላላቅ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ እና በስጋ ዶሮዎች እርባታእና ማቀነባበር ስራ ላይ ፍላጎት ያላቸውን አርቢዎች (ለምሳሌ፤ ወጣቶችን፤ ስራ-አጥ ሴቶችን፤ ወዘተ) በማደራጀት ስልጠና በመስጠት ወደ ተግባር እንዲገቡ ማስቻል
- በእንስሳት ሃብት የእንስሳት ጤና ሬጉላቶሪ በኩል ለአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ የዶሮና ዶሮ ምርት ማቀነባበሪያዎች የግንባታና አደረጃጀት ዲዛይን እንዲወጣለት ማድረግ፤
- ለምርት ማሸጊያ የሚውሉ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅና ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ የምርቱንጥራትና ደህንነት በአግባቡ ማስጠበቅ፤
- አማራጭ የአመጋገብ ሥርዓትን ለማስፋን የዶሮ ምርቶችን በቀላሉ አዘጋቶ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ ሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ

ፖሊሲ:- የዶሮ ምርት ስታንዳርዶች እንዲወጡ ይደረጋል

ስትራቴጂዎች

- የዶሮ ምርት ስታንዳርዶችን ማዘጋጀት፣የማቅረብና ማስተዋወቅ ስራ መስራትና በወጣው ስታንዳርድ መሰረት ምርቱ እየተዘጋጀ መውጣቱን ማረጋገጥ ደረጃ ያልወጣላቸውን ምርቶች በመለየት ደረጃ እንዲወጣላቸው ማድረግ

- በየትኛውም የምርት መሸጫ ቦታ ህጋዊ ፈቃድ ከሌለውና የመለያ ምልክት የሌለው ምርት እንዳይሸጥ ቁጥጥር በሚመለከተው አካል እንዲካሄድ ማድረግ

- የእሴት ጭማሪ በዶሮ አስተራረድ፣ ምርት አስተሻሸግ ፣ ምርት ማከማቸት፣ ማጓጓዝና ለተጠቃሚዉ ማድረስ ላይ ትኩረት በማድረግ በአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ የዶሮና ዶሮ ምርት ማቀነባበሪያ በሚል የመለየት ስራ ይካሄዳል

- ህገወጥ የዶሮ ስጋ አምራቾችን የሚቆጣጠርና የግብይት ስርአቱን መስመር የሚያስይዝ የህግ ማእቀፍ እንዲወጣ ማድረግ
- በዘርፉ የተሰማሩ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ለማበረታታትና ተወዳዳሪነትን ለማሻሻል ላልተወሰነ ግዜ የሚቆይ የታሪፍ ከለላና የረዥም ግዜ የብድር አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ ማመቻቸት
- የዶሮ ስጋ ማቀነባበር ተግባር በተደራጀ የዶሮ ቄራ እና ደረጃውን በጠበቀ ማቀነባበሪያ ብቻ እንዲሆን ይደረጋል

ፖሊሲ:- የዶሮ ምርት ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር አሰራር እንዲጠናከር ይደረጋል

ስትራቴጂ

- የስጋ ምርቶቹ ከ zoonosis፣ የእንስሳት መድሀኒትና ሆርሞን ቅሪት፣ አፍላቶክሲን፣ የፀረ አረምና ተባይ ኬሚካሎች ነፃ መሆናቸውና የዘረመል ልውጥ ያልተካሄደባቸው መሆናቸውን በእንስሳት ጤና ሬጉላቶሪ በኩል ማረጋገጥ የሚቻልበት አሰራር ማስፈን
- የዶሮ ስጋ ከውጭ አገር ከመግባቱ በፊት የማስገቢያ ፍቃድ (import permit) እና የጥራት ደህንነት የሚረጋገጥበት ከሚመለከተው አካል የሚጠየቅበት አሰራር መዘርጋት
- በምርት ጥራትና ቁጥጥርን በተመለከተ የሚመለከታቸው አካላት በቅንጅት የሚሰሩበት ስልት ተግባራዊ ማድረግ
- የዶሮ ምርቶችንመልካም አመራረት፣ ሀይጅን አጠባበቅ፣ አያያዝና ስርዓትና HACCP የመሳሰሉ የጥራት ማረጋገጫ ስርዓት ማንዋሎች ማዘጋጀትና ድርጅቶቹ ተግባራዊ እንዲያደርጉ አስፈላጊውን ቁጥጥር ማካሄድ
- የዶሮ ምርቶችንጥራትና ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የመስክ መፈተሻ መሳርያዎች አቅርቦት ማሳደግ
- የዶሮ ምርትን ከቦታ ቦታ ለግብይት ማንቀሳቀስ ለዚሁ ስራ በተዘጋጀ ማቀዝቀዣ በተገጠመለትተሽከርካሪ ብቻ እንዲሆን ክትትል ማድረግ
- የምርት ጥራትና ቁጥጥር ስራ ላይ ከተሰማራው ተቋም ጋር በየተወሰነ ወቅት የመረጃ ልውውጥ በማካሄድ ከሚገኘው ግብረ መልስ በመነሳት ከባለድርሻአካላት ጋር ምክክር መድረክ በማዘጋጀት የልምድ ልውውጥ መድረክ ማዘጋጀት
- የምርቱ አቀራረብ (Packaging) የሚስብና ምርቱን ረዥም ግዜ ጠብቆ ለማቆየት የሚችልእንዲሆን በማድረግከውጭ በከፍተኛ ምንዛሪ የሚገባውን ምርት መተካት
- የዶሮ ምርት ከጥራትና ደህንነት ችግሮች ነፃ ስለመሆኑ ለማረጋጥ የሚያስቸል የጥራት መመርመርያ ላቦራቶሪ እንዲቋቋም ማድረግ
- ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ምርትና ተዋፅኦ አቅርቦት እንዲኖር አስገዳጅ የምርቶች ደረጃ የማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ
- የሀገር ውስጥ ምርቶች በአግባቡ ተመርተው ተገቢው የማሸግያና ገላጭ ጽሁፍ ተደርጎላቸው ንፅህናቸው በተጠቀበቀ ሁኔታ ለገበያ የሚቀርቡበት ሁኔታ መፍጠር
- የእንስሳት ምርቶችና ተዋፅኦዎች አቅርቦት ለማሳደግና ጥራትና ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስፈልጉ ጥናቶችና ምርምሮች በጋራ ማካሄድ

ፖሊሲ:- የዶሮ ምርት ስነምግብ ይዘት፣ አጠቃቀምና አዘገጃጀት የህብረተሰብ ግንዛቤ የማሳደግ ስራ ይሰራል

ስትራቴጂ

- የተለያዩ የዶሮ ምርቶች አዘገጃጀት ማኑዋሎች እንዲዘጋጁ በማድረግ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ
- በማስ ሚዲያ በመጠቀም ስነምግብ ይዘት፣ የምርት አዘገጃጀትና አጠቃቀም ላይ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ይሰራል
- ለት/ቤቶች ምርት የሚቀርብበትን ሁኔታ ማመቻቸት

ፖሊሲ:- የስጋ ደሮ ጫጩት አቅርቦት ችግር ለመፍታት የሚያስችል አሰራር እንዲኖር ይደረጋል

ስትራቴጂ

- በየክልሉ የሚገኙትን የብዜት ማዕከላትና በዚህ ሥራ ሊሰማሩ የሚችሉ ግለሰቦችን አቅም በማሳደግ የስጋ ደሮ ዝርያዎችን መስራች ዘርየሚይዙበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- በሂደት ሥራውን ለባለሃብቶች የሚያስተላልፉበትና ማዕከላቱ መሰረተ-ርቢይዘው መስራች ዘር ለሌሎች አርቢዎች የሚያቀርቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

**6.6.** ምርምርና ቴክኖሎጂ ስርጸት ትስስር ማጠናከር

የሀገራችን የዶሮ እርባታ እርባታ ዘርፍ ከ 90.5 ፐርሰንት በላይ የሚሆነዉ በጭሮሽ እርባታ ሥርዓት ላይ የተመሰረተ፣ እጅግ ኋላ ቀር የአረባብ ዘዴ የሚከተልና ዝቅተኛ የምርታማነት ደረጃ ያላቸው የሀገረ ሰብ ዶሮ ዝርያዎችን በመያዝ የሚካሄድ በመሆኑ በብዙ ችግሮችና በበርካታ ተለያይነት ባላቸዉ ሁኔታዎች ማለትም በአረባብ ስርዓት፣ በእርባታዉ ዓላማ፣ በግባት አቅርቦት፣ በዓየር ጸባይ፣ በክህሎት ደረጃ፣ እና በሌሎች ተዛማጅ ባህርያት የሚገለጽ ነዉ። እነኚህ መጠነ ሰፊ ችግሮችና የሁኔታዎች ተለያይነት ያለበት የዶሮ ልማት ዘርፍ ለማቃናት የተጠቃሚዉ ህብረተሰብ የልማት ጥያቄን መሠረት ያደረገና በምርምር የተደገፈ አሰራርን መከተል ያስፈልጋል። በምርምር ያልተደገፈ የቴክኖሎጂ የማላመድና የመጠቀም አካሄድም ሀገርን የሚጎዳ እንጂ የሚጠቅም ሆኖ መወሰድ እንደሌለበት ከበፊት ከብዙ ተሞክሮዎች መረዳት አያዳግትም።

ሆኖም ግን እስካሁን ባለዉ ሁኔታ በሀገራችን የዶሮ ቴክኖሎጂዎች የማፍለቅና ከዉጭ አስገብቶ የማላመድ ስራዎች በተለያዩ የምርምር፣ የልማትና የግል ተቋማት እየተተገበሩ ቢሆንም የተሻሻሉ ዝርያዎች አቅርቦትና ተደራሽነት እጅግ አናሳ ነው። በተጨማሪም በእስካሁን የዶሮ ቴክኖሎጂ ማፈለቅ፣ ማባዛትና ማሰራጨት ሂደት ዉስጥ በሚሳተፉ በተለያዩ ተቋማት መካከል የታየዉ ቅንጅታዊ አሰራር ደካማ ነዉ። ለዚህም ድክመት አስተዋፅጸ ካደረጉ ጉዳዮች መካከል የሥራ ድርሻ የባለቤትነት ጥያቄ እንደ አንድ ዋነኛ ምክንያት መጥቀስ ይቻላል። ይኸውም እስካሁን በነበረዉ አሰራር ምርምር እንደ ምርምር ቴክኖሎጂን የማፍለቅና የማስተዋወቅ፣ እንደዚሁም የግብርናና የእንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ደግሞ በምርምር ተቋማት የፈለቁ ቴክኖሎጂዎች የማባዛትና የማሰራጨት ኃላፊነት

ለየብቻቸዉ ይዘዉ ይጓዙ ስለነበረ እጅግ በጣም ብዙ በምርምር የፈለቁ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ እጅ ሳይደርሱ የተቀመጡበት ሁኔታ ይታያል።

ስለሆነም የሀገሪቱ የዶሮ ሀብት ልማት ዉጤታማና ቀጣይነት እንዲኖረዉ ለማድረግ በሀገሪቱ የሚገኙ የግብርና ምርምር ማዕከላት፣ የቴክኖሎጂ ማባዣ ጣቢያዎች እንደዚሁም በዘርፉ የተሰማሩ ማህበራትና የግል ተቋማት በማደራጀትና በማጠናከር በሀገር ውስጥ የዶሮ ዝርያዎች የማሻሻል፣ የማባዛትና የማሰራጨት እንዲሁም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች የማላመድ ሥራዎች በቅንጅት መተግበር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ይህ አካሄድ ለመተግበር የሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫ እንደሚከተለዉ ተቀምጧል።

ፖሊሲ፡- በሀገሪቱ የዶሮ ምርምርና ስርጸት ስርዓት በማጠናከር፣ ለአካባቢ ተስማሚ የሆኑ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እንዲፈልቁና የፈለቁ ወይም በማላመድ የተገኙ ቴክኖሎጂዎች በተቀናጀና ቀጣይነት ባለዉ መልኩ ለህብረተሰቡ ጥቅም ይዉላሉ።

ስትራቴጂዎች፡-

ሀ. በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የምርምርና ልማት ተቋማት የዶሮ ቴክኖሎጂ አቅርቦት አቅም እንዲዳብርና እንደአስፈላጊነቱ አዳዲስ ጣቢያዎችም ማቋቋም፣

ለ. ምርምር የተጠቃሚዉን ህብረተሰብ የልማት ጥያቄን ያገናዘበና የሀገር በቀል እዉቀት መሠረት ያደረገ እንዲሆን ማድረግ፤

ሐ. ከዉጭ ለማላመድ የሚገቡ የዶሮ ቴክኖሎጂዎች ወደ ተጠቃሚዉ ህብረተሰብ ከመሰራጨታቸዉ በፊት በተቀናጀ መልኩ የተላምዶና የምርታማነት ፍተሻ ሙከራዎች ማካሄድ፣

መ. በዶሮ ቴክኖሎጂ ማፍለቅ፣ ማላመድ፣ ማስተዋወቅና ማሰራጨት ሰንሰለት ዉስጥ የሚሳተፉ እንደ የምርምርና የግብርና ተቋማት መካከል ያለዉ የቴክኖሎጂና የመረጃ ልዉዉጥ እንደዚሁም አብሮ የመስራት ግንኙነት ቅንጅታዊ እንዲሆንና እንዲጠናከር ማድረግ፣

ሠ. የዶሮ ቴክኖሎጂ የሚያፈልቁ ወይም የሚያላምዱ የመንግስት የምርምር ተቋማት ተክኖሎጂ የማፍለቅና የማላመድ እንደዚሁም የማስተዋወቅ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የፈለቁ ወይም በማላመድ የተገኙ ተክኖሎጂዎች የማባዛትና የማሰራጨት ባለቤትንም እንዲኖራቸዉና ከግብርናና እንስሳት ሚኒስቴር ጋር በመናበብ በቅንጅት እንዲሰሩ ማድረግ።

ረ. አብዛኛዉ የሀገሪቱ አርሶ አደር በምርምር የፈለቁ ወይም በማላመድ የተገኙ የዶሮ ዝርያዎች በሚፈልገዉ መጠን ለመግዛት የፋይናንስ ችግር ስላለበት ቴክኖሎጂዎችን የአርሶ አደሩ የፋይናንስ አቅም ባገናዘበ ሁኔታ ለህብረተሰቡ እንዲዳረስ ማድረግ።

**6.6.** በዶሮ እርባታ የማህበረሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ስለማሳደግ

የአርቢዉ ማህበረሰብ ሙሉ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

በሀገራችን ትልቁን ቦታ የሚይዘዉ የዶሮ ዕርባታ የጭሮሽ አረባብ ዘዴ በመሆኑና ይህም በአነስተኛ አርሶአደሮች ዘንድ የሚገኝ በመሆኑ አርሶ አደሮች በዶሮ ዕርባታ ዘንድ ያላቸዉ ዕምቅ የሀገር በቀል ዕዉቀትና የዶሮ ዝርያዎች ባለቤት ስለሆኑ ይህ ኃላቀር የአረባብ ዘዴ ለማሻሻል በሚደረጉ የምርምርና ልማት ሥራዎች ሰፊዉን ህብረተሰብ ማለትም ዶሮ አርቢ አነስተኛ አርሶአደሮች ያገናዘበ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በተጨማሪም የምርምርና የልማት ሥራዎች በዶሮ ርቢ ዘርፍ ከእርባታ እስከ ገበያ ሰንሰለት የሚሳተፉ ሌሎች ተጠቃሚዎችም ያገናዘበ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል፡፡ ይህም ለማድረግ የሚከተለዉ የፖሊሲ አቅጣጫ ማስቀመጥ አስፈልጓል፡፡

ፖሊሲ፡- የዝርያና ሌሎች የዶሮ ቴክኖሎጂዎች ማፍለቅ፣ ማላመድ እና ማሻሻል ሥራ የሰፊዉ የዶሮ አርቢዉን ማህበረሰብ ሙሉ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ያረጋገጠ ይሆናል፡፡

ስትራቴጂዎች፡-

ሀ. የዶሮ አርቢዉ ህብረተሰብ በዶሮ ዕርባታ ላይ ያለዉ ሀገር በቀል ዕዉቀትና በተመራጭነት በያዛቸዉ ልዩ የዶሮ ዝርያዎች ከግምት ባስገባ መልኩ ለአካባቢዉ ስነ-ምህዳር ተስማሚ የሆነ የአረባብ መርሀግብር እንዲተገበር ድጋፍ ማድረግ፣

ለ. በተለያዩ በዶሮ ቴክኖሎጂዎች የማፍለቅ፣ የማላመድ እና የማሻሻል ስራዎች ላይ የዶሮ አርቢዉ ህብረተሰብ በባለቤትነት እንዲሳተፍ ማድረግ፣

ሐ. በምርምር የሚፈልቁ ወይም በማላመድ የሚገኙ የዶሮ ዝርያዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ለአነስተኛ ገበሬዎች የሚደርስበት ሁኔታ ማመቻቸት፣

**6.6.1.** በዶሮ እርባታ የሴቶችና ወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

የዶሮ እርባታ ከሌሎች የእንስሳት እርባታ በተለየ መልኩ አነስተኛ ወጪ የሚጠይቅና ድሃ አርሶ አደሮችና የገጠር ሴቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚያደርግ እና በዶሮ እርባታ ሴቶች ከፍተኛዉን የስራ ድርሻ እንደሚያበረክቱ በዘርፉ የተካሄዱ በርካታ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ነገር ግን በሀገር አቀፍ ደርጃ በዶሮ እርባታ ዘርፍ የሚከናወኑ የምርምርና የልማት ሥራዎች ሴቶችንና ወጣቶች አሳታፊ ቢሆኑም የተሳትፎዉ መጠን በቂ ነዉ ለማለት አያስደፍርም፡፡ ስለዚህ በዶሮ ልማትና ምርምር ዘርፍ የሴቶችና ወጣቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት የበለጠ ለማጉላትና ቀጣይነት እንዲኖረዉ ለማድረግ የሚከተለዉ ፖሊሲ ተቀምጧል፡፡

ፖሊሲ፡- በመንግስትና በግል ተቋማት እንደዚሁም በግብረ-ሰናይ ድርጅቶች የሚካሄዱ የዶሮ የልማትና የምርምር መረሀ-ግብሮች ሴቶችንና ወጣቶች በባለቤትነት ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡

ስትራቴጂዎች፦

ሀ. በሀገራችን በሚገኙ በተለያዩ የዶሮ የአረባብ ስርዓቶች ዉስጥ ሴቶችንና ወጣቶችን ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች መለየት፣

ለ. በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚተገበሩ የዶሮ ልማትና ምርምር ሥራዎች ሴቶችና ወጣቶች እንዲሰተፉ ማድረግ፣

ሐ. በምርምር የሚፈልቁ ወይም በማላመድ የሚገኙ የዶሮ ቴክኖሎጂዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ለሴቶችና ወጣቶች የሚደርስበት ሁኔታ ማመቻቸት፣

**6.6.2.** የዶሮ አርቢ ማህበራት ስለማደራጀት

በዶሮ እርባታ ላይ የተሰማሩ አነስተኛ አርሶአደሮችና ኢንተርፕራይዞች ያሉባቸዉ መጠነ ሰፊ ችግሮች ሊቀርፉባቸዉ ከሚያስችሏቸዉ ዘዴዎች አንዱ በማህበር መደራጀት ነዉ። ይህ ዘዴ በተለይ ለዶሮዎቻቸዉ ግባት ለማቅረብ፣ ለምርቶቻቸዉ ገበያ ለማፈላለግ፣ እና ያሉባቸዉ ችግሮች በጋራ ሆነዉ ለሚመለከተዉ ለመንግስት አካል ለማሰማት እጅግ በጣም ጠቃሚ ነዉ። አሁን ባለዉ ሁኔታ በሀገር ዉስጥ በዶሮ ዘርፍ የተሰማሩ ማህበራት ቢኖሩም ቁጥራቸዉና ሙያዊ ብቃታቸዉ በቀጣይነት ለማዳበር የሚከተለዉ የፖሊሲ ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

ፖሊሲ፦ በሀገሪቱ በዶሮ እርባታ፣ ምርት ማቀነባበርና ገበያ ዘርፍ የሚሰማሩ ማህበራት እንዲጠናከሩና እንዲደራጁ ይደረጋል።

ስተራቴጂዎች፦

ሀ. በዶሮ እርባታና የዶሮ ምርቶች ማቀነባበር ላይ የተሰማሩ ማህበራት ሙያዊ ብቃታቸዉ በስልጠና እንዲዳብር ማድረግ፣

ለ. ማህበራት በዝርያና በሌሎች የዶሮ ተክኖሎጂዎች የማባዛትና ማሰራጨት ሥራዎች ላይ ማሳተፍ፣

ሐ. ማሕበራት በሀገሪቱ የዶሮ ልማት ዘርፍ የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ ከፍ ለማድረግ ተጨማሪ አዳዲስ ማህበራት ማቋቋም፣

መ. ነባር ወይም አዳዲስ የዶሮ ማህበራት የኢንቨስትመንት መጠናቸዉ ከፍ ለማድረግና ለማዘመን ከተለያዩ የፋይናንስ ምንጮች ብድር የሚያገኙበት ሁኔታ ማመቻቸት፣

ሠ. በተጨማሪም የዩንቨርስቲ ተመራቂዎች በማህበር እየተደራጁ በተቀናጀ የዶሮ እንዱስትሪ ስራ ላይ እንዲሰማሩ የሚደረግበትን ሁኔታ ማመቻቸት

**6.6.3.** በዶሮ ርቢ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎችን ስለማበረታታት

የሀገሪቱ የዶሮ ልማት ለማዘመን አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች አንዱና ዋንኛ ቦታ የሚሰጠዉ ለእንቁላል፣ ሥጋ ወይም ጥምር ጠቀሜታ ያላቸዉ የዶሮ ዝርያዎች ማግኘት ነዉ። ይህ ደግሞ ሊገኝ የሚችለዉ በሀገር ውስጥ በመረጣ በማሻሻል ወይም ከዉጭ አስገብቶ በማላመድ ነዉ። ይህ አይነቱ የቴክኖሎጂ የማመንጨት ሥራ በተነጻጻሪነት ረጅም ጊዜ የሚወስድና በአንዴ ተጀምሮ የሚቋረጥ ሳይሆን በቀጥይነት መካሄድ የሚገባዉና ትግስት የሚጠይቅ ስራ ነዉ። በሌላ በኩል ደግሞ የግል ባለሃብቶች የዶሮ ቴክኖሎጂ በማፍለቅም ሆነ በማላመድ ሥራ ላይ በአጭር ጊዜ ትርፍ መሰብሰብ ስለማይችሉ የሥራ ዘርፉ ብዙም ደፍረዉ ሲገቡበት አይታዩም። ስለዚህ በሀገራችን የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች በሚፈለገዉ መጠንና ቀጣይነት ባለዉ መልኩ እንዲኖር ለማስቻል በዘርፉ ልምድና ዕዉቀት ያላቸዉ ባለሞያዎች እንዲሰማሩ ማበረታታት አንዱ መፍትሄ ነዉ። ከዚህም አኳያ በዘርፉ የሚገኙ ባለሞያዎች በዶሮ ዝርያ ማፍለቅና ማላመድ ሥራ ላይ በግልም ሆነ በጋራ በመቀናጀት እንዲሰማሩ ለማስቻል የሚከተለዉ ፖሊሲና የማስፈጸሚያ ስትራቴጂ ተቀምጧል።

ፖሊሲ፦ ለእንቁላል፣ ሥጋ ወይም ጥምር ጠቀሜታ ከፍተኛ ምርት ሊሰጡ የሚችሉ የዶሮ ዝርያዎች በሀገር ዉስጥ ማፍለቅ ወይም ከዉጭ አስገብቶ ማላመድ ስራ ላይ የዘርፉ ባለሞያዎች በግልም ሆነ በጋራ በመደራጀት ሊሰማሩ ይችላሉ፤ ድጋፍም ይደረጋል።

ስትራቴጂዎች፦

ሀ. ከዝርያ በተያያዘ በባለሞያዎች በግልም ሆነ በጋራ ሊተገበሩ የሚችሉ የስራ መስኮች መለየት፣

ለ. ባለሞያዎቹ በዝርያ ማፍለቅ ወይም ማለመድ ሥራ ላይ መሰማራት እንዲችሉ አስፈላጊዉ የብድርና ሌሎች የበጀት ድጋፍ እንደዚሁም የመሬት አቅርቦት ማመቻቸት፣

ሐ. ከዉጭ የተሻሻለ የዶሮ ዝርያ ወደ ሀገር ዉስጥ አስገብቶ በማላመድ መጠቀም ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ባለሞያዎች የዉጭ ምንዛሪ እንዲያገኙ ትብብር ማድረግ፣

መ. በዶሮ ዝርያ ማፍለቅና ማላመድ ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ባለሙያዎች ካፒታላቸዉ እንዲያሳድጉና ቀጣይነት ያለዉ ሥራ እንዲሰሩ ከዝርያ ማመንጨትና ማላመድ ጎን ለጎን ሌሎች የፋይናንስ ማመንጪያና አቅም ማሳደጊያ ስራዎች እንዲሰሩ ፈቃድ የሚያገኙበት ሁኔታ ማመቻቸት።

**6.7.** አቅም ግንባታን በተመለከተ

በአጠቃላይ በዶሮው ልማት ዘርፍ ከሚነሱት ፈታኝ ችግሮች አንዱ በዶሮ እርባታ፤ አያያዝ፤ ጤና አጠባበቅ እና በምርት ማቀነባበር ሙያ የሰለጠነ የሰው ኃይል በበቂ ያለመገኘት ነው።

ፖሊሲ፦ በዶሮ ምርት ፕሮሰሲንግ የሰለጠነ የሰው ኃይል የማፍራት ስራ ይካሄዳል

ስትራቴጂ

- በኮሌጆችና በዩንቨርስቲዎች በዶሮ ምርት ማቀነባበር (በሁሉም የዶሮ እርባታ እሴት ሰንሰለት)ትምህርት ካሪኩለም እንዲዘጋጅ በማድረግ ምሩቃንን የማፍራት ስራ ይካሄዳል
- ደረጃቸውን የጠበቁ የማሰልጠኛ ማኑዋሎች በማዘጋጀት በደሮ ምርቶች ማቀነባበር አጫጭር ስልጠናበሚመለከታቸው ተቋማት እንዲሰጡ ይደረጋል
- እንዲሁም እንዱስትሪ ዩንቨርስቲ ትስስር እንዲጠናከር ማድረግና በተጨማሪም የዩንቨርስቲ ተመራቂዎች በማህበር እየተደራጁ በተቀናጀ የዶሮ እንዱስትሪ ስራ ላይ እንዲሰማሩ የሚደረግበትን ሁኔታ ማመቻቸት

የምርምር አቅም፡

ፖለሲ፡- የሀገሪቱ የዶሮ ሀብት ልማት ዘርፍ ወቅታዊና የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ባደረጉ ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎች በመደገፍ ከዘርፉ የሚጠበቀውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽ ማበርከት የሚያስችልየምርምር አቅም ይገነባል።

ስትራቴጂ፡-

የሀገሪቱ የዶሮ ምርምር ፕሮግራም በሰለጠነ የሰው ሀይል፣ በዘመናዊ የእርባታ መሳሪያዎች እና በተደራጁ ላበራቶሪዎች የታገዘ የዶሮ ምርምር የልቀት ማዕከል እንዲሆን ማስቻል፣

**6.8.** ግብይት

የዶሮና የዶሮግብይትበአርሶ አደሮች፤በግል ዶሮ አርቢዎች፣ በአቀናባሪዎች በእንተርፕራይዞች በሆቴሎች እና ሱፐር ማርኬቶች መካከል የሚካሄድ ግብይት ነው።የሀገር ውስጥ የዶሮና የዶሮ ምርት ፍላጎት ከአቅርቦት አንጻር ሲታይ ከጊዜ ወደ ጊዜ ልዩነቱ እየሰፋ ከመምጣቱ ባሻግርከፍተኛ የጥራትና የዘላቂ አቅርቦት ክፍተት እንዳለበት መረጃዎች ይጠቁማሉ። የሕገ-ወጦች መበራከትና የዶሮ ና የዶሮ ምርት ዋጋ እንደ ወቅቱ የሚዋዥቅመሆኑና በአያያዝ ጉድለት ሳቢያ ወደ ገበያ የሚደርሰው ምርት ጥራት አነስተኛ መሆን ስርዓት ውስጥ የሚታዩ ተግዳሮቶች ናቸው።

ፖሊሲ:- ዶሮ እና የዶሮ ምርት ግቢይት የእሴትና ግብይት ሰንሰለቱን የጠበቀ፤ በግብይትተዋናዮች መካከል ዘመናዊ የግቢይት ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል።

ስትራቴጂ

- በዶሮ ግብይት ሥርዓት ዉስጥ በዶሮና ዶሮ ምርት ላይ እሴት በመጨመር ወይም በማቀነባበር (Poultry Processing) የግል ባለ ሀብቱ በስፋትእንዲሳተፍ ይበረታታል
- የዶሮ እና የዶሮ ምርት ግቢይት ጥራትና ደረጃውን የጠበቀና የግብይት ሥርዓትን የተከተለ እንዲሆን የዶሮ ምርት ጥራት ደረጃዎች እንዲዘጋጅ ይደረጋል
- የዶሮ እና የዶሮ ምርት ገበያ እንደየአከባቢ ሁኔታእንዲደራጅ ይደረጋል እንዲሁም የግብይት ሥርዓትም እንዲዘረጋ በትኩረት ይሠራል
- ዶሮ እና የዶሮ ምርቶች አግባብ ባልሆነ መንገድ ወደ ጎረቤትና ሌሎች ሀገሮች እንዳይላኩ ቁጥጥር ይደረጋል
- የምርት ተጠቃሚውና አምራቹ በአጭር የገበያ ስርአት እንዲገናኙ ማስቻል
- ህጋዊ የስጋ ዶሮ ጫጩት አቅራቢዎች የዶሮ ማርባት ፍቃድ ለሌላቸው ሰዎች ጫጩት እንዳያቀርቡ ክትትል ማድረግና የስራና የንግድ ፍቃድ አሰጣጥና እድሳት ቅድመ ማጣሪያ ማድረግ
- በገበያ እየቀረበ ያለው የዶሮ ስጋ ተገቢው ታክስ ተከፍሎበት ወደ ገበያ የገባ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ አካል እንዲኖር ማድረግ

ፖሊሲ፡- የዶሮና ዶሮ ምርት ገበያ መረጃ ልውውጥ ስርዓት ይዘጋጃል።

ስትራቴጂ

- በመንግስት በኩል ከተለያዩ ግብይት ማዕካለት እና እርሻዎች የዶሮና ዶሮ ምርት ገበያ ዋጋ መረጃ እየተሰበሰበ እና እየተጠናከረ ለሕብረተሰቡ የሚደርስበት መንገድ ማመቻቸት
- በዶሮ ሀብት ልማት የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች ሥራቸዉንና ምርታቸዉን የሚያስተዋዉቁበት መድረክ፣ ባዛር፣ ኤግዚቢሽን ይዘጋጃል።

## 6.9. መሰረተ ልማት

ፖሊሲ፡- የዶሮ ሀብት ልማት መሰረተ ልማት እንዲስፋፋ ይደረጋል

ስትራቴጂዎች

- በዶሮ ምርት ማምረትና ማቀነባበር ለተሰማሩ ግለሰቦች፣ ባለሀብቶች፣ የመንግስት ማባዣ ማዕከላት ለእርባታ የሚሆኑ ተስማሚ መሰረተ ልማቶች(ሙብራት፣መንገድና ውሀ) አቅርቦት ተደራሽ ይሆናሉ።
- የእንቁላል ማቀነባበር ስራ ላይ የግል ባለሀብቶች እንዲሳተፉበት አስፈላጊውን መረጃ የማቅረብና ኢንቨስትመንቱን ማበረታታት

- የጥራት ምርመራ ላቦራቶሪዎች ማደራጀት (የስነ ህይወት ደህንነትና ፕሮቶኮል ማዘጋጀትና የቁጥጥር ስራ መስራት)
- መስራች ዘር ያላቸው ማዕከላት በውስጣቸው እናት ዶሮ ቤት፣ ጫጩት ማሳደጊያ፣ ማስታቀፊያና ማስፈልፈያ፣ መኖ ማልሚያ ቦታ፣ መኖ ማቀነባበሪያና ማከማቻ፣ የታመሙ ዶሮዎች ማቆያ፣ ምርት መሸጫ እንዲሁም ለስጋ ዶሮ ማዕከላት የዶሮ ቄራና መቆያ እንዲኖረው ማድረግ
- የተለያዩ የእንስሳት ምርቶችና ተዋጽኦዎች የቅዝቃዜ ሰንሰለታቸው ተጠብቆ ከአቅራቢዎች ለመሰብሰብ እንዲሁም ምርቶች ወደ ገበያ ለማጓጓዝ የሚያስችሉ የተለያዩ የቅዝቃዜ ሰንሰለት ማስጠበቅያ ቴክኖሎጂዎች በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያገኙበት ሁኔታዎች ማመቻቸት
- የሀገር ውስጥ የጫጩት አቅርቦትን የበለጠ አስተማማኝ ለማድረግና ከውጭ የሚገባውን የወላጅ ዶሮች ለማስቀረት ቅድመ ወላጅ ዶሮች የሚይዙ መስራች ዶሮ ዘር ማራቢያ ማዕከላት ተገንብተው ወደ ስራ እንዲገቡና ለመንግስትም ሆኑ ለግል ማባዣ ማዕከላት ወላጅ ዶሮችን በለማ እንቁላል ደረጃ እንዲያሰራጩ በማድረግ በዶሮ እርባታ መሠረተ ልማት ዘርፍ ፈጣን ለውጥ እንዲመጣ ይሰራል።
- እነዚህንከወላጅዶሮችማዕከላትተባዝተውየሚወጡትንጫጩቶችተቀብለውበማሳደግ በብዛትና በጥራት አምርተው የሚያሰራጩ ነባርማሳደጊያዎችእንዲጠናከሩናአዳዲስ ማዕከላት እንዲቋቋሙ ይደረጋል።
- ደረጃውን የጠበቀ የዶሮና ዶሮ ምርት ማጓጓዣ አገልግሎት የሚሰጡ የግል ተቋማት የሚፈጠሩበት ሁኔታ የማመቻቸት ስራ ይሰራል
- ተንቀሳቃሽ የዶሮ ቄራ አገልግሎትን በማስተዋወቅ በክላስተር የእርድ አገልግሎት የሚሰጥበት ሁኔታ የማመቻቸት ተግባር ይከናወናል።

### **6.10.** ኢንቨስትመንት

በሀገሪቱ ያለው የዶሮ ሀብት ልማት በአብዛኛው በአርሶ አደሮችና በባህላዊ የአረባብ ዘዴ ያለ ከመሆኑ አንጻርበእንስሳት ሀብት ልማት ፍኖተ ካርታና በእድገትና ትራንስፎርሜሽኑ እቅድ ላይ የተመላከተውን የልማት ግቦች ላይ ለመድረስኢንቨስትመንቱ የሚስፋፋበት ስርአት መዘርጋት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ይህን ከግብ ለማድረስ የሚከተለው ፖሊሲ አቅጣጫ ተቀምጧል።

ፖሊሲ፡- በዶሮ ሀብት ልማት ለሚሳተፉ የግል ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል።

ስትራቴጂዎች

- የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በዶሮ ልማት ዘርፍ በዋናነት ትኩርት በሚሹ ዘርፎች ማለትም በመኖ ልማት፤ በዝርያ ማፍለቅ ፤ማላመድ ፤ማባዛትና ማሰረጨት እንደዚሁም በመድህኒትና ክትባት አቅርቦት እንዲሳተፉ ማድረግ
- የአገሪቱን የዶሮ ልማት ዘርፍ በፍጥነት ለመለወጥ በሚያስችሉ በተመረጡ የግብርና ሞዴሎች (የኮንትራት ግብርና እና የዶሮ መንደር) ዘርፍ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት እንዲያካሂዱ ድጋፍ ማድረግ
- በግሉ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች የአካባቢውን ማህበረሰብ ከመደገፍ አንጻር ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ ይደረጋል
- በዘርፉ ለተሰማሩና በአዲስ መልኩ ለሚሰማሩ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ከውጭ በሚያስገቡበት ሰዓት ከቀረጥ ነጻ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ
- የተቀናጀ ዶሮ ሀብት ልማት ላይ ለሚሳተፉ ድርጅቶችም ሆነ ግለሰቦች ለኢንቨስትመንት የሚሆን መሬት(ለዶሮ ማርቢያ፤ለመኖ ማልሚያና ለምርት ማቀነባበሪያ) በሚያቀርቡት ጥናት መሰረት በቀላሉ ማግኘት የሚችሉበትን አሰራር መተግበር
- ለዘርፉ መስፋፋት ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር አኳያ የብድር አገልግሎትን ቀልጣፋ ማድረግ
- ለሁሉም አርቢዎች ለተወሰነ ግዜ የሚቆይ የግብር እፎይታ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ
- በአዲስ መልኩ ወደ ፕሮሰሲንግ ለመግባት ፍላጎት ላላቸው ባለሀብቶች በየክልልሉ በተቋቋሙ አግሮ ፕሮሰሲንግ ፓርክ ውስጥ ገብተው እንዲሰሩ አስፈላጊውን መረጃ አደራጅቶ መስጠት
- በዶሮ ሀብት ልማት ለሚሳተፉ የመድን ዋስትና ሽፋን እንዲያገኙ ማድረግ
- ከውጭ የተለያዩ ለዶሮ ሀብት ልማት በግብዓትነት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችም ሆኑ የተሻሻሉ ዝርያዎች ፣ፕሪሚክስና የመሳሰሉትን ወደ አገር ውስጥለሚያስገቡ የውጭ ምንዛሪ በተቀላጠፈ መንገድ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት

## 6.11. ተጓዳኝ ጉዳዮች

### *6.11.1* ሥርዓተ ጾታ

ከሀገራችን አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት ሴቶች ሃምሳ በመቶ ያክል የሚሸፍኑ ቢሆንም የልማት ተሳታፊነታቸውና ተጠቃሚነታቸው ፍትሐዊ እንዳልሆነ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በአንጻሩ የዶሮ ሀብት ልማት ለብዙ ሴቶች ፣ የቤተሰብ መሪ ለሆኑ እማወራዎችና ሥራ አጥ ወጣቶች ከፍተኛ የሥራ ዕድል ሊፈጥር የሚችል የሥራ ዘርፍ ነው። በመሆኑም ይህ የዶሮ ሀብት ልማት ፖሊሲ ፍትሐዊ የሆነ ሥርኣተ ጾታ እንዲሰፍንና የሴቶችና ወጣቶች የልማት ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት እንዲኖር በሚያስችል ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ ሴቶች በመጠኑም ቢሆን በቤተሰብ ዶሮ እርባታ፣ በአነስተኛና መካከለኛ ንግድ ተኮር የዶሮ እርባታ ስርዓት ውስጥ እየተሳተፉ ይገኛሉ፤ ይሁንና ዘርፉ በርካታ ችግሮች ስላሉበት በታሰበው ልክ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ ማድረግ አልተቻለም ። በመሆኑም

በዘርፉአዎቂ ሰዎችና  አካል ጉዳተኞች ይካተቱየሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተስማሚ ፓኬጆችና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎቸን በማቅረብና በመደገፍ፣ የብድር አገልግሎት ስርዓት በመቅረጽና በማመቻቸት እንዲሁም የገበያ መረጃ እንዲኖር በማድረግ ሴቶች በዘርፉ በሚፈጠረው የሥራ እድል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

**6.11.2.** የአካባቢ ጥበቃ እና የማህበረሰብ ደህንነት

እንስሳት በተለይም ትላልቅ አመንዣኪ እንስሳት፣ ሙቀት አማቂ ጋዞችን ወደ ከባቢ አየር በመልቀቅ ለአለም ሙቀት መጨመር ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። በአንጻሩ ከዶሮዎች የሚለቀቀው ሙቀት አማቂ ጋዝ) እጅግ በጣም አናሳ ነው። ስለዚህ የዶሮ ሥጋ ምርትን ከአጠቃላይ ሀገራዊ ሥጋ ምርት አሁን ካለበት 5% ድርሻ በ2023 ወደ 30% በማሳደግ ከትላልቅ አመንዣኪ እንስሳት የሚለቀቀውን ሙቀት አማቂ ጋዝ በመቀነስ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም አረንጓዴ ልማት ለማረጋገጥ አውንታዊ አስተዋጽኦ ማበርከት ይቻላል።

በተጨማሪም በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የዶሮ ሀብት ልማት ሥራ የእንስሳትን የውጪ ንግድ ለማጠናከርና የህብረተሰቡን የፕሮቲን ፍላጉት በቀላሉ ለማሟላት ትልቅ ድርሻ እንዳለው ይታወቃል። ይሁንና የዶሮ እርባታው ኢንዱስትሪ ወደ ፊት እያደገና እየተስፋፋ ሲመጣ የዶሮ ቤት ቆሻሻ እና የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርት ለአካባቢ ብክለት እንዳያጋልጥ የእንስሳት አያያዝን ማሻሻል፣ እንዲሁም በዘመናዊ መንገድ በማስወገድና ፕሮሰስ በማድረግ ጥቅም ላይ መዋል የሚችሉትን መንገድ ማመቻቸት ፤ እንዲሁም መንግስትና የሚመለከታቸው አካላት ያለውን የሀገሪቱን የአካባቢ ጥበቃ ህግ ከዘርፉ እድገት ጋር በየጊዜው በመቃኘት ማሻሻልና ከዶሮ ኢንደስትሪ የሚወጡ ተረፈምርቶችን በአግባቡ መጠቀምን በማበረታታት አካባቢ እንዳይበከል እና ማህበራዊ ችግር እንዳይፈጥር ከፍተኛ ጥበቃ ይደረጋል።

### 6.11.3. ሥነምግብ

አምራችና ጥሩ ዜጋ ለመፍጠር ከሥነ ምግብ ውስጥ  ፕሮቲንና ሃይል ሰጪ ምግቦች ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። በዚሁ መሠረት  የዶሮ ሥጋና እንቁላል ከፍተኛ የፕሮቲን ይዘት ካላቸው ምግቦች የሚመደቡ የምግብ ዓይነቶች ናቸው። ይሁን እንጂ በሀገራችን በተለያየ ሥነ-ምህዳር ለረቡ የሚችሉ የዶሮ ዝርያዎች ቢኖሩም ምርታማነታቸው ዝቅተኛ ነው። በሌላ በኩል በተለይ ከፕሮቲን እጥረት በመነጨ የህጻናት ሞት፤ መቀጨጭና መቀንጨር እንዲሁም የበሽታ መስፋፋት በሰፊው በሀገራችን የሚታዩ ችግሮች ናቸው። ከሌሎች የግብርና ዘርፎች ሲነጻጸር የዶሮ ዕርባታ ዘርፍ ትኩረት ከተሰጠው ይህንን ችግር በቀላሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመፍታት ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል። ከዚህ በመነሳት መንግስት በዶሮ ሀብት ልማት ላይ ያተኮረ የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርት ማሻሻያ ሥራዎችን ይደግፋል።

በተጨማሪም ህብረተሰቡ ባለው አነስተኛ ግንዛቤና በአንዳንድ አካባቢዎች ባለው የባህል ተጽህኖ ምክንያት በሀገራች የዶሮ ስጋና እንቁላል አጠቃቀም እጅግ አናሳ ሆኖ ይገኛል። በመሆኑም በዶሮ ስጋና እንቁላል አያያዝ፣ አጠቃቀም ፣ አዘገጃጀትና አመጋገብ እንዲሁም ለሰው ልጅ የሚሰጠው የስነ ምግብና የጤና ጥበቃ ላይ የተለያዩ የማስተዋወቅ፣የማስተማርና ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎችን በሰፊው በማከናወን የህብረተሰቡ የዶሮ ስጋና እንቁላል አመጋገብ ስርዓት እንዲያድግ ይደረጋል።

መንግስት የነደፈውን ሥነ ምግብን መሠረት ያደረገ ግብርና መርሃ ግብር ተግባራዊ ለማድረግ ትኩረት ከሚደረግባቸው የግብርና ዘርፎች አንዱ የዶሮ ዕርባታ ሥራ ሲሆን፣ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ውጤት ለማምጣት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ይሠራል። በዚህ መሠረት መንግሥት የተለያዩ አዳዲስ የዶሮ ልማትን ሊያግዙ የሚችሉ የሥነ ምግብ ምርጥ ተሞክሮዎች እንዲቀመሩ፣ የምግብ ማዘጋጃ ቴክኖሎጂዎች እንዲፈጠሩና እንዲስፋፉ ያደረጋል፡

### 6.11.4. የአገር በቀል ዕውቀት

የአገር በቀል እውቀትን ለመጠቀምና ለማጎልበት አርሶ አደሩ በተለይ ለአካባቢ ዶሮ ዝርያዎች ዓይነትና ባህሪያቸው እንዲሁም የእርባታ ዘዴአቸው ያለው ዕውቀትና ክህሎት ተለይቶ እንዲታወቅ፣ እንዲመዘገብና ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል። እንዱሁም ህብረተሰቡ  ለዶሮናዶሮ ምርት አጠቃቀም ላይ ያለውን የተሳሳተ ግንዛቤ ለማስተካከል ይሠራል።

## 7. ከፖሊሲው የሚጠበቅ ውጤት

ብሔራዊ የዶሮ ሀብት ልማት ፖሊሲ በኢትዮጵያ ተግባራዊ ሲሆን የሚከተሉት ውጤቶች ይጠበቃሉ።

- ለሀገሪቱ የግብርና ሥነ-ምህዳር እና የአረባብ ሥርዓት ተስማሚ የሆነና ጥራቱን የጠበቀ የዶሮ ዝርያ አቅርቦት ቀጣይነት ባለው መልኩ ለአርሶ አደሩ እና ለዶሮ አርቢዎች ማህበረሰብ የሚቀርብበት ሁኔታ ይመቻቻል።

- በዶሮ መኖ ጥሬ ዕቃ ማምረት ለሚሰማሩ ግለሰቦች፣ ባለሀብቶች እና ማህበራት የቦታ አቀርቦት፣ ብድር እና ምቹ የሥራ ሁኔታ ይመቻቻል
- ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የዶሮ መኖ ለአርቢው ማህበረሰብ በበቂ መጠንና በተመጣጣኝ ዋጋ ይቀርባል
- ጥራት ያለው የዶሮ በሽታ ክትባቶች፣ መድሐኒቶች እና ሌሎች የእንስሳት ጤና ግብዓቶች አቅርቦት ሽፋን እንዲሁም የዶሮ ጤና አገልግሎት ሽፋን ይጨምራል
- የዶሮ ምርትን በጥራት ለማምረት የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች የመጠቀም ዕድል ይሰፋል፣ እንዲሁም ዶሮና የዶሮ ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ይስፋፋሉ።
- ህብረተሰቡ እሴት የተጨመረባቸው የዶሮ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ያገኛል
- ለተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ለሥራ አጥ ወጣቶች፣ ሴቶች ፣ መሬት የሌላቸው አ/አደሮች ሰፊ የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡
- የተጠናከረና የተቀናጀ የዶሮ ሀብት ልማት ምርምር እና ቴክኖሎጂ ስርጸት ይፈጠራል፡
- ተስማሚ፣ አዋጪ፣ ችግር ፈቺ አማራጭ ቴክኖሎጂዎች በመርምር ይፈልቃሉ
- በፕሮቲን እጥረት ምክንያት የሚከሰተውን የህጻናት መቀንጨር ለመቀነስና የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት አስተዋጽኦ ያበረክታል
- የዶሮ እርባታ ማሰልጠኛ ተቋማትና ማባዣ ማዕከላት ይስፋፋሉ፤
- ለዶሮ ሀብት ልማት ዘርፍ የተሟላ የመሠረተ ልማቶች አቅርቦት ይኖራል፤
- ፍትሐዊ የሆነ የዶሮ እና ዶሮ ምርት ገበያ ሥርዓት ይፈጠራል፤
- በዶሮ ሀብት ላይ መዋለ ንዋያቸውን ለሚያፈሱ ባለ ሀብቶች የማበረታቻ ስርዓት ተግባራዊ ይሆናል፤
- ደረጃውን የጠበቀ ዶሮና የዶሮ ምርት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ይቀርባል
- በዶሮ ሀብት ልማት የሰለጠነ ብቁ የሰው ሀይል አቅርቦት ይኖራል፤
- ህብረተሰቡ የዶሮ ምርትን በተለያየ መንገድ ለምግብ በማዘጋጀት የመጠቀም ባህሉ ይዳብራል።

## 8. ተቋማዊ ሁኔታና የህግ ማዕቀፍ

### 8.1. ተቋማዊ አደረጃጀት

በግብርናና እንስሳት ሀብት ልማት ሚኒስቴር የእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ የዶሮ ሀብት ልማትስራ በሀገር ውስጥ የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ በዘርፉ ለተሰማሩ የግልና የመንግስትማዕከላት፣ የምርምር ተቋማት፣ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እንዲሁም ለአርሶና/አርብቶ አደሩምቹሁኔታ በመፍጠር ዘርፉን ውጤታማ የማድረግ ሀላፊነት አለበት።የእንስሳት ጤናና ጥራትቁጥጥር ዘርፍ የዶሮ ሀብት ልማት ላይ በሽታ እንዳይከሰት መከላከልና መቆጣጠር፣ከውጪ ወደሀገር ውስጥ የሚገቡና ከሀገር የሚወጡ ዶሮና የዶሮ ምርቶችን፣ የዶሮ መኖና መድሀኒት ጥራትንመቆጣጠር ሀላፊነት አለበት። የግብይት ዘርፉ ዶሮና የዶሮ ምርት ግብይትን የማቀላጠፍተልእኮ ተቀብሎ እየሰራ ይገኛል።

ይህም በሁለቱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት መካከል ምንም አይነት ቅንጅት ባለመኖሩ በቀጣይበዘርፉ ላይ ችግር ይፈጥራል የሚል ስጋት አለ። ተቋሙ በተቀመጠለት ተልኮ መሰረት በክልል፣በዞንና ወረዳ እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉ ስራዎችን ያስተባብራል ይከታተላል ይደግፋል። ነገርግንይህንን ተልእኮ መፈጸም የሚያስችል ወጥ የሆነ አደረጃጀት በክልሎች ባለመኖሩ ከዘርፉየሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት አስቸጋሪ እንዲሆን አድርጎታል። የዶሮ ምርምር በግብርናምርምር ኢንስቲትዩት ቢሰራም የዶሮ ምርምር ስራው በሚፈለገው መጠን የዘርፉን ችግርእየፈታ አለመሆኑና በምርምርና ስርጸት መካከል የተጠናከረ የቴክኖሎጂ ቅብብሎሽ ስርዓትአለመኖር እንዲሁም በሚኒስትሩ እና ከሚኒስትሩ መስሪያ ቤት ውጪ በዶሮ ሀብት ልማት ስራላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ቅንጅት አነስተኛ በመሆኑ በዘርፉ አፈጻጸም ሂደት ላይ ተጽህኖእየፈጠረ ይገኛል።

በመሆኑም በቀጣይ ማንኛውም ዶሮና የዶሮ ምርት እንዲሁም የመጀመሪያ ደረጃ የዶሮ ምርትቁጥጥር በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር የእንስሳት ጤና ዘርፍ ሀላፊነት ይተገበራል።የክልል አደረጃጀት ወጥ በሆነና ለስራው መፋጠን በሚያግዝ መልኩ ይደራጃል። የቴክኖሎጂአቅርቦትና ሽግግርን ለማሻሻል በተቋማት መካከል ያለው ትስስር እንዲጠናከር ይደረጋል።ስራዎችን በተጠናከረ መልኩ ለማስተባበር የሚያስችል የዶሮ ሀብት ልማት ቦርድ እንዲቋቋምይደረጋል። በተጨማሪም ዘርፉ በዶሮ ሀብት ልማት የተለያዩ የሙያ ማህበራትን የማደራጀትየማጠናከርና የመደገፍ ተልዕኮ እንዲኖረው ይደረጋል።

### 8.2. የግል ተቋማት

የተለያዩ የግል ተቋማት አምራቾች፣ ግብዓት አቅራቢዎች፣ አበዳሪ ተቋማትና መንግስታዊያልሆኑ ድርጅቶች በዘርፉ በመሳተፍ በዶሮ ሀብት ልማት እድገት ውስጥ ጉልህ ድርሻ እያበረከቱእንዳለ ይታወቃል። ነገርግን የእነዚህ የተለያዩ አካላት ስራ በአግባቡ የተቀናጀ ባለመሆኑአብዛኞቹ በተመሳሳይ ስራ ላይ በመሰማራት አላስፈላጊ የስራ መደራረብ እየተፈጠረ ይገኛል።በተጨማሪም የግል ተቋማት መንግስት በዶሮ ሀብት ልማት ያቀደውን እቅድ ከ70 በመቶ በላይእንደሚያሳኩ ታሳቢ የተደረገ ቢሆንም ጠንካራ የሆነ የኤክስቴንሽን ድጋፍና ክትትል ከመንግስትእያገኙ ባለመሆኑ ዘርፉ ላይ የሚፈለገው ለውጥ ሳይመጣ ቆይቷል። በተጨማሪም የግል ተቋማትየሚሳተፉባቸው መስኮች ውስን መሆናቸውም የራሱ ተጽህኖ እንዳለው ይታሰባል።

በመሆኑም የግል ዘርፉ በዶሮ ልማት በግብዓት አቅርቦት፣ በህክምና፣ በዝርያ ማባዛት፣ በምርምር፣በዶሮና ዶሮ ምርት ማቀነባበር፣ እንዲሰማራ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል። የግል ተቋማትንበተቀናጀና በተበታተነ መልኩ ለመምራት የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል እንዲሁም የተጠናከረየኤክስቴንሽን አገልግሎትና ድጋፍ ይሰጣል።

## 9. የበጀት ድጋፍ

### 9.1. ለመንግስት ተቋማት የሚደረግ የበጀት ድጋፍ

በሀገር ደረጃ የዶሮ ልማትን ማስተባበር መከታተልና መደገፍ እንዲሁም የምርምርና ጥራትቁጥጥር ስራዎች በመንግስት የሚተገበሩ ሲሆን ነገርግን በቂ በጀት ባለመኖሩ ዘርፉየሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ ሳያበረክት ቆይቷል። በተጨማሪም ከዚህ በፊት አንዳንድ ስራዎችበፕሮጀክት ቢጀመሩም ቀጣይነት ስለማይኖራቸው ይህነው የሚባል

ለውጥ ማምጣት አይችሉምበመሆኑም በዘርፉ የግል ባለሀብት ቢገባ አዋጭ ባልሆነባቸው፣ ለሀገራችን አዳዲስ በሆኑናኢንቨስትመንት በሚፈልጉ ነገርግን ወሳኝ የሆኑ ፕሮጀክቶችለምሳሌ የግራንድ ፓረንት እስቶክ ማዕከል፣የጥራት መመርመሪያና መፈተሻ ላብራቶሪዎችና ቁሳቁሶች መንግስት አስፈላጊውን ድጋፍና ኢንቨስትመንት ባለማድረጉ በርካታ የዘር ጫጩቶች በውጪ ምንዛሬ ከውጪ እንዲገቡ እየተደረገ ይገኛል። ይህም ለከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ ፍላጎት ዳርጎናል፣የአቅርቦት ውስንነት ፈጥሯል፣ አንዳንድ በሽታዎች በምልልስ ወደ ሀገር ሊገቡ እንደሚችል ሥጋት ሲፈጥር ቆይቷል።በተጨማሪም ደረጃቸውን ያልጠበቁ ምርቶች ለገበያ የሚቀርብበት ሁኔታ እየተፈጠረ ይገኛል።በመሆኑም በቀጣይ ከዘርፉ የሚገኘዉን ጠቀሜታ ለማሳደግና አስተማማኝ ለማድረግ እንዲቻል መንግስት ለምርምር ለልማትና ኤክስቴንሽን፣ ለቁጥጥር ስራ፣ለመሠረተ ልማት ግንባታና ለልዩ ልዩ ግብዓቶች ግዢ የሚሆን በቂ በጀት እንዲመድብ ይደረጋል።በተጨማሪም መንግስት ወሳኝ በሆኑና ለግል ዘርፉ አዋጭ ባልሆኑ ስራዎች ላይ ኢንቨስት በማድረግ ከውጪ የሚገቡ ግብዓቶችን ለመቀነስና ችግሮችን ለመቅረፍ ይሰራል።

### **9.2.** ለግል ተቋማት የሚደረግ የበጀት ድጋፍ

ምንም እንኳን በአንዳንድ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የፋይናንስ ተቋማት የመነሻ የገንዘብ ብድር የሚሰጥ ቢሆንም በመጠንም ሆነ በተደራሽነት አነስተኛ በመሆኑ፣ብድሩንም ለመውሰድ የሚጠየቀውን ማስያዣ ማቅረብ ባለመቻልና ብድሩን ለመመለስ የሚሰጠው የእፎይታ ጊዜ ከእርባታ ስራው ጋር ግምት ያልተወሰደ በመሆኑ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች በተለይም በአነስተኛ ደረጃ በየእሴት ሰንሰለቱ የተሰማሩ ሴቶችና ወጣቶች የሚፈለገውን ውጤት እንዳያመጡ እያደረጋቸው ይገኛል።በተጨማሪም በሀገራችን ለእንስሳት ሀብት ልማት የመድህን ዋስትና ሽፋን የሌለ በመሆኑ ባንኮች የሚፈለገውን ብድር ለመስጠት አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል።

በመሆኑም በደሮ እርባታ ስራ ላይ በየእሴት ሰንሰለቱ በአነስተኛና በትላልቅ ደረጃ ለሚሰማሩ ግለሰቦች፣ማህበራት እና አርሶና/አርብቶ አደሮች የተለያዩ ብድር አቅርቦት አማራጮች እንዲስፋፉ ይደረጋል።ዘርፉ በሚፈለገው መልኩ ምቹ የብድር አቅርቦት እንዲኖር የሚያስችል ስልት ይቀየሳል፣ለዶሮ ምርትና ግብይት ብድር የሚሰጡ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማትና ህብረት ስራ ማህበራት እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ይደረጋል።የብድር አገልግሎቱም የተሳለጠ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

## **10.** ክትትልና ግምገማ

የተዘጋጀው ብሔራዊ የዶሮ ሀብት ልማት ፖሊሲ አተገባበር ሂደት የታለመለትን ዓላማ ያሳካ እንዲሆን ቀጣይነት ባለው መልኩ መቆጣጠርና መገምገም ያስፈልጋል።ለዚህም አስተማማኝ የሆነ የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት በየጊዜው የሚገኘውን ውጤት ለማወቅ እንዲሁም ተጠያቂነትና ግልፀኝነትን ማዳበር ያስፈልጋል።ከዚህም በተጨማሪ ፖሊሲ ፈፃሚ አካላት እየተገበሩ ያሉት የፖሊሲ አፈፃፀም ድክመቶችን ለማረምና ጥንካሬዎችን በማጎልበት በመረጃ የተደገፈ ውሣኔ ለመስጠት የክትትልና ግምገማ ስርዓት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

በመሆኑም የፖሊሲዉን አፈፃፀም በወቅቱ ለመከታተል፣ለመገምገምና እንደ አስፈላጊነቱ የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ስርዓት ይዘረጋል።ይህም ዘርፉን ማዕከል በማድረግ ከታችኛው

የአስተዳደር እርከን እስከ ፌደራል ባሉ ፈፃሚ አካላት የተሰበሰቡ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ አፈጻጸሙ ይገመገማል።ለዚህም እንዲረዳ በየዓመቱ የሚጠበቁ ዓመታዊ ዒላማዎች ዝርዝር የሚያሳይ የተግባር አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ይቀርባል። በዚህ ማዕቀፍ የተቀመጡትን መረጃዎች በተቀላጠፈና አስተማማኝ መንገድ ለመቀባበል የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብና ማስተላለፊያ ስርዓት ይዘረጋል።ስርዓቱም በሚመለከታቸው ተቋማት በቅንጅት የሚተገበር ይሆናል።

በፖሊሲዉ ትግበራ ዘመን በፌደራልና በክልል አስፈፃሚ አካላት የክትትልና የግምገማ ስርዓቱን በተገቢው መንገድ ለማስፈፀም የሚያስችል የአቅም ግንባታሥራ መስራት እንዲሁም የሰው ኃይል በበቂ ሁኔታ ማሰማራት ያስፈልጋል።